Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 21
ADDIS ABABA 2nd April, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፯/፪ሺ፲፫

የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት አዋጅ ....................ገጽ ፲፫ሺ፶፩

## Content

Proclamation No. 1237/2021

Arbitration and Conciliation, Working Procedure Proclamation ……………………………Page 13051

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፯/፪ሺ፲፫**

**የግልግል ዳኝነትን እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ**

የግልግል ዳኝነትና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት መዘርጋቱ የአለመግባባት መፍቻ አማራጮችን በማስፋት ፍትሕ የማግኘት መብትን ለማሟላት አጋዥ በመሆኑና በተለይም የኢንቨስትመንትና ንግድ ነክ አለመግባባቶችን ለመፍታት እና ለዘርፉ እድገት አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ፤

የግልግል ዳኝነት እና ዕርቅ የተዋዋይ ወገኖችን ወጪ በመቀነስ፣ ምስጢርን በመጠበቅና ልዩ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎች በዳኝነት እንዲሳተፉ በማድረግ እንዲሁም ቀላልና ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት ያለው ሥነ ሥርዓት ለመጠቀም በመፍቀድ የተቀላጠፈ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ፤

የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ በግልግል ዳኝነት የሚታዩ ጉዳዮችን ለመለየት፣ ሂደቱ የሚመራበትን እና ውሳኔ የሚፈጸምበትን አጠቃላይ ማዕቀፍ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO.1237/2021**

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR ARBITRATION AND CONCILIATION.WORKING PROCEDURE**

**WHEREAS,** the establishment of Alternative Dispute Resolution and Conciliation helps to complement the right to justice and, in particular, contribute to the resolution of investment and commercial related disputes and to the development of the sector;

**WHEREAS,** arbitration and conciliation help in rendering efficient decision by reducing the cost of the contracting parties, protecting confidentiality, allowing the participation of experts and the use of simple procedure which provides freedom to contracting parties;

**WHEREAS,** it is necessary to provide for a general framework for the identification of arbitrable cases, management of arbitration proceedings and execution of decision by taking into account the objective condition prevailing in the country;

ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ አጋዥ በመሆኑ፤

ከግልግል ዳኝነትና ከዕርቅ ጋር በተያያዘ የዳበሩ ዓለም አቀፍ አሠራሮችንና መርሆችን ታሳቢ በማድረግ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፯/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"የግልግል ዳኝነት ስምምነት"** ማለት ከውል ወይም ከውል ውጭ ባለ ሕጋዊ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችልን ወይም የተፈጠረን አለመግባባት በሙሉ ወይም በከፊል በግልግል ዳኝነት ለመፍታት የሚፈፀም ስምምነት ነው፤

፪/ **"የግልግል ዳኝነት ውሳኔ"** ማለት አለመግባባቶችን ለመፍታት በቋሚነት በተደራጀ የግልግል ተቋም ወይም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በጊዜያዊነት በሚቋቋም የግልግል አካል የሚሰጥ ውሳኔ ነው፤

**WHEREAS**, the Proclamation helps in implementing international treaties acceded and ratified by Ethiopia;

**WHEREAS**, it has become necessary to amend the laws in force by taking into account the international practices and principles related to arbitration and conciliation;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## SECTION ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arbitration and Conciliation Working Procedure Proclamation No. 1237 /2021".

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Arbitration Agreement"** is an agreement to be implemented in order to partly or wholly settle future or existing dispute that may arise from contractual or non-contractual legal relationship;

2/ **"Arbitral Award"** means a decision rendered by a permanent arbitral institution or by an ad hoc arbitral body formed by the agreement of contracting parties;

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፫/ **"የግልግል ዳኝነት ማዕከል"** ማለት በመንግሥት ወይም በግል ባለቤትነት የሚቋቋም ሆኖ የግልግል ዳኝነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፣

፬/ **"ፍርድ ቤት"** ማለት መደበኛ የዳኝነት ሥልጣን ያለው በሕግ የተቋቋመ አካል ነው፣

፭/ **"ጉባዔ"** ማለት አንድ ዳኛ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች የሚሰየሙበት የግልግል ዳኞች ስብስብ ነው፣

፮/ **"የግልግል ዳኛ"** ማለት በተዋዋይ ወገኖች ወይም በሦስተኛ ወገን የሚሰየም ገለልተኛ የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው፣

፯/ **"ንግድ ነክ"** ማለት የንግድ ባህሪ ካላቸው ከውል ወይም ከውል ውጭ ባሉ ግንኙነቶች ሁሉ የሚመነጩ ሆነው፣ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ወይም ለመለዋወጥ የሚደረግ የንግድ ግንኙነት፣ ለማከፋፈል የሚደረግ ስምምነት፣ የንግድ ወኪልነትን፣ ኪራይን፣ የግንባታ ሥራን፣ የማማከር ሥራን፣ የምህንድስና ሥራን፣ ለንግድ ጉዳይ የሚደረጉ የፈቃድ ጉዳዮች፣ የኢንቨስትመንት፣ የፋይናንስ ሥራ፣ የባንክ ሥራ፣ ኢንሹራንስ ፣የማዕድን ሥራዎች፣ በዚህ አዋጅ ከተከለከሉት ውጭ ያሉ የእሽሙር እና ሌሎች ንግድ ማህበራት ጉዳዮች፣ በአየር፣ በባህር ወይም በየብስ የሚደረጉ የሰው እና ዕቃ የማጓጓዝ ሥራዎች እና የመሳሰሉትን ያካትታል፣

3/ **"Arbitration Center"** means a Center to be established by government or under private ownership to provide arbitration service;

4/ **"Court"** means an organ established by law with regular judicial power;

5/ **"Tribunal"** means a sole arbitrator or a panel of more than one arbitrator;

6/ **"Arbitrator"** means an impartial natural person to be designated by contracting parties or third party;

7/ **"Commercial Related"** includes business relationship for the supply and exchange of goods or services, agreement for distribution, commercial agent, lease, construction, consultancy, engineering, license for commercial purpose, investment, finance, bank, insurance, mining; joint venture and other business organizations that are not prohibited by this Proclamation, transportation of persons and goods by air, sea and land and includes similar businesses arising from contractual or extra-contractual relations of a commercial nature;

፰/ **“በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ”** ማለት ኢትዮጵያ ባፀደቃቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት በውጭ ሀገር እንደተሰጠ የሚቆጠር የግልግል ውሳኔን ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ በውሳኔው ውስጥ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ መሆኑ የተገለፀበት ውሳኔ ነው፤

፱/ **“ዕርቅ”** ማለት ተዋዋይ ወገኖች በሚመርጡት ሶስተኛ ወገን አጋዥነት ከውል ወይም ከውል ውጪ በሚመነጭ ሕጋዊ ውጤት ባለው ጉዳይ ላይ በክርክር ሂደት ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችልን አለመግባባት ለመፍታት የሚያከናውኑት ሂደት ነው፤

፲/ **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩/ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ይህ አዋጅ ንግድ ነክ በሆኑ ብሔራዊ የግልግል ዳኝነቶች፣ መቀመጫቸውን ኢትዮጵያ ባደረጉ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነቶች ላይ እና ብሔራዊ በሆኑ የዕርቅ ሂደቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰፣ ፱፣ ፳፭፣ ፳፮፣ ፳፯፣ ፶፩፣ ፶፪፣ እና ፶፫ ድንጋጌዎች መቀመጫቸውን ከኢትዮጵያ ውጭ ባደረጉ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

8/ **”Foreign Arbitral Award”** means an arbitral award which is deemed to have been rendered in a foreign country in accordance with international treaties acceded and ratified by Ethiopia or a decision in which the seat of arbitration is mentioned to be outside of the Ethiopian territory;

9/ **“Conciliation”** is a process facilitated by a third party designated by contracting parties in order to resolve existing or future dispute that may arise from contractual or non-contractual legal relationship;

10/ **“Person”** means a natural person or juridical person;

11/ Any expression in the masculine gender includes the feminine;

## 3. <u>Scope of Application</u>

1/ Without prejudice to the International Treaty to which Ethiopia is a signatory, this Proclamation shall apply to commercial related national arbitration, international arbitration whose seat is in Ethiopia and national conciliation proceedings.

2/ Notwithstanding the Provision of Sub Article (1) of this Article, the Provisions of Article 8, 9, 25, 26, 27, 51, 52 and 53 of this Proclamation shall apply to International arbitration situated outside of Ethiopia.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፫/ ከተዋዋይ ወገኖች መካከል አንዱ መኖሪያውን ወይም የቢዝነስ መቀመጫውን ኢትዮጵያ ያደረገ ከሆነ እና የግልግል ዳኝነት መቀመጫው ባልተሰየመበት የግልግል ዳኝነት ሂደት ላይ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪፣ ፲፬፣ ፲፮ እና ፲፯ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

3/ The Provisions of Articles 12, 14, 16, and 17 of this Proclamation shall apply where the principal residence or the principal business place of one of the contracting parties is situated in Ethiopia and where the place of arbitration is not designated.

## ፬. ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት

፩/ አንድ የግልግል ዳኝነት ከዚህ በታች ከተመለከቱት በአንዱ ሥር የሚወድቅ ከሆነ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት እንደሆነ ይቆጠራል፡-

ሀ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ስምምነት በሚፈጽሙበት ወቅት ዋነኛ የቢዝነስ ቦታቸው በሁለት በተለያየ ሀገራት የነበረ ሲሆን፣

ለ) በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የተመረጠ የግልግል ዳኝነቱ ሕጋዊ መቀመጫ ወይም፣ በንግድ ወይም በውል ግንኙነቱ ውስጥ ያሉ ዋነኛ ግዴታዎች የሚፈፀሙባቸው ወይም አለመግባባቱ የተከሰተበትና የተያያዘበት የተዋዋይ ወገኖች ዋነኛ የቢዝነስ ቦታ ውጭ ሀገር ሲገኝ፣

ሐ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ጉዳይ ከአንድ በላይ በሆኑ ሀገሮች ጋር የተያያዘ መሆኑን በግልፅ ሲስማሙ፡፡

## 4. International Arbitration

1/ An arbitration shall be deemed to be International arbitration if it falls under one of the following:

a) Where the principal business place of the contracting parties are in two different countries at the time of the conclusion of the agreement;

b) Where the legal place of the arbitration chosen in accordance with the arbitration agreement or the place of the principal business where the substantial part of the obligations of the commercial or contractual relationship is to be performed or the place of business with which the subject-matter of the dispute is arised and most closely connected is located in a foreign country;

c) Where the parties have expressly agreed that the subject-matter of the arbitration agreement relates to more than one country.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል ተዋዋይ ወገኖች ከአንድ በላይ የቢዝነስ ቦታ ያላቸው ሆኖ ሲገኝ ለግልግል ስምምነቱ ቅርበት ያለው የቢዝነስ ቦታ እና ምንም የቢዝነስ ቦታ የሌላቸው ከሆነ የተዋዋይ ወገኖች መደበኛ መኖሪያ ቦታ እንደ ዋነኛ የቢዝነስ ቦታቸው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

2/ If a party has more than one place of business for the purpose implementing this Article, the place of business shall be that which has the closest to the arbitration agreement and, where there is no place of business, it will be the principal residence of the contracting parties.

## ፭. <u>የፍርድ ቤት ጣልቃ ገብነት ስለመከልከሉ</u>

ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተለይቶ ከተሰጣቸው ሥልጣን በስተቀር፣ በግልግል ዳኝነት በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ አይገቡም፡፡

## 5. <u>Prohibition of Intervention by the Court</u>

Court shall not intervene in arbitrable matters except where it is specifically provided for in this Proclamation.

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>የግልግል ዳኝነት ስምምነት</u>

# <u>SECTION TWO</u>

# <u>ARBITRATION AGREEMENT</u>

## ፮. <u>የግልግል ዳኝነት ስምምነት ፎርም</u>

፩/ የግልግል ዳኝነት ስምምነት በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡

፪/ የግልግል ዳኝነት በጽሁፍ እንደተደረገ የሚቆጠረው በቃል፣ በድርጊት ወይም በሌላ አኳኋን የተደረገ ቢሆንም ይዘቱ ተመዝግቦ የሰፈረ፣ በሁሉም ተዋዋይ ወገኖች እና ሁለት ምስክሮች ሲፈረምበት ነው፡፡

፫/ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ የተደረገ የግልግል ስምምነት መረጃው በተፈለገ ጊዜ ጥቅም ላይ ለማዋል ተደራሽ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ የጽሁፍ ፎርም እንዳሟላ ይቆጠራል፡፡

፬/ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ የሚደረግ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ውል ተቀባዩ ስምምነቱን በገለፀበት ቦታ እንደተፈፀመ ይቆጠራል፡፡

## 6. <u>Forms of Arbitration Agreement</u>

1/ Arbitration agreement shall be in writing.

2/ The arbitration agreement shall be deemed to have been made in writing where its content is recorded, signed by all parties and two witnesses even where it was made orally, by conduct or any other means.

3/ An arbitration agreement concluded by electronics media shall be deemed to have been made in written form where it is accessible for use when the information is needed.

4/ An arbitration agreement entered through electronic media shall be deemed to be concluded at a place where the offeree gives his consent to the agreement.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፭/ ለዚህ አንቀፅ ዓላማ “የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት” ማለት ማንኛውም በኢሜይል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ወይም በኤሌክትሮኒክ፣ በማግኔቲክ፣ በኦፕቲካል ወይም ተመሳሳይ በሆኑ ዘዴዎች ተዋዋይ ወገኖች የሚያደርጉት የመረጃ መላክ፣ መቀበል ወይም ማከማቸት ተግባር ነው፡፡

5/ For the purpose of this Article, ‘Electronic Communication’ means any exchange of information between the contracting parties through email or the act sending, receiving and storing of information through electronic, magnetic, optical or similar means.

## ፯. ለግልግል ዳኝነት የማይቀርቡ ጉዳዮች

የሚከተሉት ጉዳዮች ለግልግል ዳኝነት አይቀርቡም፡-

፩/ የፍች፣ የጉዲፈቻ፣ የአሳዳሪነት፣ የሞግዚትነት እና የውርስ ጉዳዮች፣

፪/ የወንጀል ጉዳዮች፣

፫/ የግብር ጉዳዮች፣

፬/ መክሰር ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፣

፭/ የንግድ ማሕበራት መፍረስ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፣

፮/ የሊዝ ጉዳይን ጨምሮ አጠቃላይ የመሬት ጉዳዮች፣

፯/ አስተዳደራዊ ውሎች በልዩ ሁኔታ በሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር፣

፰/ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ፣

፱/ በሕግ ለሚመለከታቸው አስተዳደራዊ አካላት በተሰጠ ሥልጣን ሥር የሚሸፈኑ አስተዳደራዊ አለመግባባቶች፣

፲/ በግልግል እንዳይታዩ በሕግ የተከለከሉ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

## 7. Non-Arbitrable Cases

The following shall not be submitted for arbitration:

1/ Divorce, adoption, guardianship, tutorship and succession cases;

2/ Criminal cases;

3/ Tax cases;

4/ Judgment on bankruptcy;

5/ Decisions on dissolution of business organizations;

6/ All land cases including lease;

7/ Administrative contract, except where it is not permitted by law;

8/ Trade competition and consumers protection;

9/ Administrative disputes falling under the powers given to relevant administrative organs by law;

10/ other cases that is not arbitrable under the law.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፰. የግልግል ዳኝነት ስምምነት እና በፍርድ ቤቶች ስለሚቀርብ ክስ**

፩/ በአንድ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ውስጥ በሚወድቅ አለመግባባት ላይ ለፍርድ ቤት ክስ ሲቀርብ እና ተከሳሹ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ያላቸው በመሆኑ በዚያው አግባብ መታየት እንዳለበት ተቃውሞውን ካቀረበ ፍርድ ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ መሠረት ጉዳያቸውን እንዲጨርሱ ሊያሰናብታቸው ይገባል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የማይፀና ወይም ተፈፃሚ የማይሆን በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ክስ በፍርድ ቤት በሂደት ላይ መሆኑ ጉባኤው የግልግል ዳኝነቱን ጎን ለጎን ከመጀመር፣ ሂደቱን ከመቀጠል እንዲሁም የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ከመስጠት አይከለክልም፡፡

፬/ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን መኖር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አለማንሳት የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን ቀሪ እንደሆነ ያስቆጥረዋል፡፡

**8. Arbitration Agreement and Suits to be Submitted to Court**

1/ Where a suit falling under an arbitration agreement is brought before a court and the defendant raises preliminary objection that the parties agreed to resolve their disputes through arbitration agreement, the court shall dismiss the suit and the parties to resolve their dispute in accordance with the arbitration agreement.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the court shall hear the case where the arbitration agreement is void and becomes ineffective;

3/ The fact that the suit mentioned in Sub-Article (2) of this Article is pending before a court does not prohibit commencement or continuation of the arbitration proceedings parallelly, and not prohibit the arbitral tribunal from rendering an award.

4/ The arbitration agreement shall be deemed null and void if it is not raised under preliminary objection.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



**፱. <u>የግልግል ዳኝነት ስምምነት እና በፍርድ ቤት የሚሰጡ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች</u>**

ተዋዋይ ወገኞች የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ወይም ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን መሠረት በማድረግ ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፤ይህንን ማድረግ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን እንደተቃረኑት፣ ፍርድ ቤቶችም ጣልቃ ገብነት እንደፈፀሙ አይቆጠርም፡፡

**፲. <u>በግልግል ዳኝነት ስምምነት ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ሕጎች</u>**

፩/ የግልግል ዳኝነቱ ስምምነትና ሂደቱ ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት የግልግል ዳኝነት ሕግ መሠረት ይታያል፡፡

፪/ መቀመጫውን በኢትዮጵያ ባደረገ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ላይ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተፈፃሚ የሚሆነውን ሕግ ያልመረጡ እንደሆነ ይህ አዋጅ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ ስምምነቱን በራሱ ለመፈጸም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም የዚህን አዋጅ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን የሚጻረር ሲሆን የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን የማይችል የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ሲያጋጥም ተዋዋይ ወገኖች በሚመርጡት ሌላ የግልግል ሕግ ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ግልግሉ ይታያል፡፡

**9. <u>Arbitration Agreement and Provisional Interim Measure taken by Courts</u>**

With respect to matters falling under the arbitration agreement, the contracting parties may request the court interim measures to be taken before the arbitration proceeding is initiated or during the proceedings. This shall not be considered as violation of the arbitration agreement by the contracting parties and as intervention by the court.

**10. <u>Laws Applicable to Arbitration Agreement</u>**

1/The arbitration agreement and the proceedings shall be governed by the arbitration law chosen by the contracting parties.

2/ This Proclamation shall be applicable to arbitration agreement in which Ethiopia is designated as a seat of the arbitration, where the contracting parties have not chosen the applicable law, as provided in Sub-Article (1) of this Article.

3/ Notwithstanding the Provision of Sub-Article (1) of this Article, the agreement of the contracting parties shall not be applicable where it is impossible to implement the agreement on its own, or where it violates the mandatory provisions of this Proclamation.

4/ Where there is an agreement of the contracting parties that cannot be implemented as provided in Sub-Article (3) of this Article, the arbitration shall be governed by other law chosen by the parties or the Provisions of this Proclamation.

## ክፍል ሦስት

## ስለ ግልግል ዳኞች ብዛት እና አሰያየም

### ፲፩. የግልግል ዳኞች ብዛት

፩/ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞቹን ብዛት በስምምነት መወሰን ይችላሉ፤ ሆኖም የዳኞቹ ብዛት ጎደሎ ቁጥር መሆን አለበት፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች የዳኞችን ብዛት በስምምነት መወሰን ያልቻሉ እንደሆነ የግልግል ዳኞች ብዛት ሦስት ይሆናል፡፡

### ፲፪. የግልግል ዳኞችን ስለመሰየም

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ መንገድ ካልተስማሙ በስተቀር ማንኛውም ሰው በዜግነቱ ምክንያት የግልግል ዳኛ ከመሆን ሊታገድ አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞች አሰያየም ሥነ-ሥርዓትን በስምምነት ሊወስኑ፣ የግልግል ዳኝነት ተቋማት ወይም ሶስተኛ ወገን የግልግል ዳኞችን እንዲሰይሙላቸው ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ የሚከተሉት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

ሀ) አንድ ዳኛ ብቻ ባለበት የግልግል ዳኝነት ሁለቱም ወገኖች በስምምነት ይመርጣሉ፤ ሦስት ዳኞች ያሉበት የግልግል ዳኝነት ላይ እያንዳንዱ ወገን አንድ ዳኛ ይመርጣል፤ ሁለቱ የተመረጡ ዳኞች በሰብሳቢነት የሚሠራውን ሦስተኛ ዳኛ ይመርጣሉ፤

## SECTION THREE

## NUMBER AND DESIGNATION OF ARBITRATORS

### 11. Number of Arbitrators

1/ Contracting parties may determine the number of arbitrators by agreement. Provided that the number of judges shall be odd number.

2/ Where contracting parties fail to agree on the number of arbitrators, there shall be three arbitrators.

### 12. Appointment of Arbitrators

1/ Unless the contracting parties agree otherwise, no person shall be precluded from being designated as an arbitrator on the basis of his citizenship.

2/ Unless provided otherwise in this Proclamation, contracting parties shall be free to agree on the procedure of appointment of arbitrators, appointment of arbitration by arbitration centers or by third party.

3/ Where the contracting parties fail to agree in accordance with Sub-Article (2) of this Article, the following shall apply:

a) Where the arbitral tribunal has one arbitrator, both parties shall mutually agree on the appointment; in the case of three arbitrators, each contracting party shall appoint one co-arbitrator; and the appointed co-arbitrators shall appoint the third arbitrator who serves as the presiding arbitrator;

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም፣አንደኛው ወገን ዳኛ እንዲመርጥ በሌላኛው ወገን ማስታወቂያ በተሰጠው በ፴ ቀናት ውስጥ ዳኛ መምረጥ ካልቻለ ወይም ሁለቱም ዳኞች ከተመረጡ በ፴ ቀናት ውስጥ የሦስተኛ ዳኛ ምርጫ ላይ መስማማት ካልቻሉ ወይም አንድ ዳኛ ብቻ ባለበት የግልግል ዳኝነት ሁለቱም ወገኖች መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ በአንደኛው ወገን ጠያቂነት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛውን ይሰይማል፡፡

b) Notwithstanding paragraph (a) of Sub-Article 3 of this Article, where one of the contracting parties fail to appoint the co-arbitrator within 30 days from the date of receipt of the notice by the other party, or where the two arbitrators fail to agree on the appointment of the third arbitrator within 30 days from the date of their appointment or where the contracting parties fail to agree, in the case of a sole arbitrator, the First Instance Court shall appoint such arbitrator upon the request of one of the parties.

፬/ የግልግል ዳኝነት ሂደቱን የጀመረ ወገን ሌላኛው ወገን የግልግል ዳኛውን በመምረጥ ሂደቱ እንዲሳተፍ ወይም በራሱ ወገን የሚመርጠውን ዳኛ መርጦ እንዲያሳውቅ በአግባቡ ማስታወቂያ ተሰጥቶት በ፴ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖሩን የካደ እንደሆነ ጠያቂው አካል የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን በራሱ ጊዜ የመሰረዝ እና ክሱን ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

4/ Where the contracting party who has initiated the arbitration has notified the other party to participate in the appointment of arbitrator or properly notified to designate a co-arbitrator from his side and if he fail to reply within 30 days or deny the existence of an arbitration agreement, the requesting party shall have the right to cancel the agreement in his own time and submit his suit to the court.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት ፍርድ ቤቱ የግልግል ዳኛ በሚመርጥበት ጊዜ በግልግል ስምምነቱ የተጠቀሱ መስፈርቶችን፣ የዳኛውን ገለልተኛነት ነፃነት እንዲሁም ከአለመግባባቱ ጋር በተያያዘ ያለውን ሙያዊ ብቃት ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

5/ When the court appoints an arbitrator in accordance with paragraph (b) of Sub-Article (3) of this Article, it shall take into account the criteria stated in the arbitration agreement and the impartiality and independence of the arbitrator as well as his professional competence in relation to the dispute.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጉዳዩ ዓለም አቀፍ የግልግል ጉዳይ ሆኖ የሚታየው በአንድ ዳኛ ብቻ በሚሆንበት ጊዜ ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ የግልግል ዳኛው ዜግነት ከተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስለመሆኑ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

6/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, where the hearing is an International arbitration hearing conducted by a sole arbitrator, it shall be taken into account that the citizenship of the arbitrator is different from either party.

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

7/ No appeal shall lie from the decision of a court rendered in accordance with paragraph (b) of Sub-Article (3) of this Article.

## ፲፫. የግልግል ዳኞች መብትና ግዴታ

## 13. Rights and Obligations of an Arbitrator

፩/ ማንኛውም ሰው ዳኛ እንዲሆን ጥያቄ ሲቀርብለት የጥቅም ግጭት፣ ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን ሊያውክ የሚችል ወይም ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሊያሳድር በሚችል ደረጃ የቤተሰብ፣ የብድር፣ የንግድ ወይም የንብረት ባለቤትነት ግንኙነት ከተዋዋይ ወገኖች ጋር ካለው ወይም ካጋጠመው ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

1/ When a person is requested for a position of arbitrator, he shall promptly notify any conflict of interest which interferes with, or casts reasonable doubt on, his impartiality and independence or if he has or discovers any family, loan, business or property ownership relationship with either of the contracting parties.

፪/ የግልግል ዳኛ ለሥራው መሰየሙን የተቀበለ እንደሆነ መስማማቱን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ Where an arbitrator accepts his designation, he shall notify his agreement in writing.

፫/ የግልግል ዳኛ የአገልግሎት ክፍያ የማግኘት እና ላወጣው ወጪ የመካስ መብት አለው፡፡

3/ An arbitrator shall have a right to receive fee for his service and to be reimbursed for his expenses.

፬/ የግልግል ዳኛ ሥራውን በቅልጥፍና መስራትና የግልግል ሂደቱ ያለአግባብ እንዳይራዘም ወቅቱን ጠብቆ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

4/ An arbitrator shall perform his function efficiently and take prompt action to prevent unnecessary delay of the arbitration proceeding.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፭/ ለግልግል በቀረበው ጉዳይ ላይ ጠበቃ፣ አማካሪ፣ አስማሚ ወይም በፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ከዚህ በፊት የተሳተፈ ሰው በዛው ጉዳይ ላይ የግልግል ዳኛ ሆኖ ማገልገል አይችልም፡፡

፮/ በግልግል ዳኝነት ሂደቱ አግባብ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የግልግል ዳኛ ተዋዋይ ወገኖችን በተናጠል ማግኘት አይችልም፡፡

፯/ የግልግል ዳኞች ከተዋዋይ ወገኞች ማንኛውንም ዓይነት ስጦታ መቀበል አይችሉም፡፡

**፲፬. <u>የግልግል ዳኞችን ስለመቃወም</u>**

፩/ የአንድን ዳኛ መመረጥ መቃወም የሚቻለው ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን ወይም በግልግል ስምምነቱ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማያሟላ መሆኑን አሳማኝ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ብቻ ነው፡፡

፪/ አንድ ወገን ራሱ በመረጠው ዳኛ ወይም በምርጫው ሂደት በተሳተፈበት ዳኛ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ የሚችለው ዳኛው ከተመረጠ በኋላ በሚያውቀው ምክንያት ብቻ ነው፡፡

**፲፭. <u>የተቃውሞ ሥነ- ሥርዓት</u>**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኞች ላይ ተቃውሞ ስለሚቀርብበት ሥነ-ሥርዓት ስምምነት ማድረግ ይችላሉ፡፡

5/ A person who has previously participated as an attorney, advisor, conciliator or judge of a court shall not serve as an arbitrator in the same case.

6/ An arbitrator shall not, unless it is found appropriate in the arbitration proceedings, meet with a contracting party separately.

7/ Arbitrators shall not accept any kind of gift from the contracting parties.

**14. <u>Objection to Arbitrators</u>**

1/ An objection against the appointment of an arbitrator may be made only if there are circumstances which create justifiable doubts as to his impartiality and independence, or fulfillment of the criteria stated in the arbitration agreement.

2/ A party may only challenge the arbitrator appointed by him or in whose appointment he has participated for reasons known to him after the appointment of the arbitrator.

**15. <u>Procedures of Objection</u>**

1/ Contracting parties may agree on the procedures of objection against the appointment of arbitrators.

፪/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ስምምነት የሌለ እንደሆነ፣ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በግልግል ዳኛ ላይ ተቃውሞ የማቅረብ ፍላጎት ያለው ወገን የግልግል ዳኛው ከተሰየመበት ወይም ለተቃውሞ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠሩ ፲፭ ቀናት ውስጥ ለመቃወም ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በጽሁፍ በመግለጽ ለጉባዔው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ ተቃውሞ የቀረበበት ዳኛ በራሱ ፈቃድ ካልተነሳ ወይም ሌላኛው ወገን በተቃውሞው ካልተስማማ ጉባዔው በቀረበው ተቃውሞ ላይ ይወስናል፡፡

፬/ ያቀረበው ተቃውሞ ውድቅ የተደረገበት ሰው ውጤቱ በተነገረው በ፴ ቀናት ውስጥ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቅሬታውን ማመልከት ይችላል፤ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

፭/ ፍርድ ቤት በተቃውሞው ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ካገደበት እለት ጀምሮ ቢበዛ በ፷ ተከታታይ ቀናት ውስጥ በተቃውሞ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

## ፲፮. ሥራን በአግባቡ ማከናወን አለመቻል

፩/ አንድ የግልግል ዳኛ በሕግ ወይም በሁኔታዎች ምክንያት ሥራውን በአግባቡ ማከናወን ካልቻለ ወይም ያለ በቂ ምክንያት ካዘገየ እና ተዋዋይ ወገኖች ከተስማሙ ከኃላፊነቱ ይነሳል፤ ተዋዋይ ወገኖች ይህንን ስምምነታቸውን ለጉባዔው በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

2/ In the absence of agreement between the parties, a party, who intends to raise objection against an arbitrator before a decision is made, shall submit the reasons of objection in writing to the arbitral tribunal within 15 days as of the designation of the arbitrator or the date he becomes aware of the causes of the objection.

3/ Unless the arbitrator against whom the objection is raised resigns willingly or the other party agrees to the objection, the tribunal shall render decision on the objection.

4/ A person whose objection is rejected may submit his grievance to the First Instance Court within 30 days from the date such decision is communicated to him. No appeal shall lie from the decision of the court.

5/ The court may order the suspension of the arbitration proceeding until it renders its decision on the objection. The court shall render decision within 60 consecutive days from the date of suspension of the proceedings.

## 16. Failure to Properly Discharge Functions

1/ An arbitrator shall, if the contracting parties agree, be removed from his position where he is unable to properly discharge his functions on legal grounds or causes delay in performance without good cause. The contracting parties shall notify their agreement to the tribunal in writing.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጉባዔው ርምጃ ካልወሰደ ወይም የግልግል ዳኛው በራሱ ፈቃድ ካልተነሳ ወይም ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ላይ ካልደረሱ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፤ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት አንድ የግልግል ዳኛ ራሱን ከዳኝነት ማንሳቱ ወይም እንዲነሳ ተዋዋይ ወገኖች መስማማታቸው ዳኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጡ ሁኔታዎችን እንደተቀበለ አያስቆጥረውም፡፡

**፲፯. <u>ተተኪ ዳኛ ስለመሰየም</u>**

፩/ አንድ የግልግል ዳኛ በማንኛውም ምክንያት ከጉባዔ እንዲነሳ በመወሰኑ ወይም ራሱ ሥራውን በማቋረጡ ከኃላፊነቱ ሲሰናበት በምትኩ ሌላ ዳኛ ይሰየማል፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች ተተኪ ዳኛ ስለሚሰየምበት ሁኔታ አዲስ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር፤ ተተኪ የግልግል ዳኛ የሚሰየመው የተቀየረው የግልግል ዳኛ በተሰየመበት ሥርዓት ይሆናል፡፡

፫/ በተነሱት የግልግል ዳኞች የታየው የግልግል ሂደት ካቆመበት እንዲቀጥል ወይም እንደ አዲስ ሂደቱ እንዲጀምር ተዋዋይ ወገኖች ሊስማሙ ይችላሉ፤ መስማማት ካልቻሉ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

2/ The contracting parties may apply to the First Instance Court where the tribunal fails to take measures pursuant to Sub-Article (1) of this Article or the arbitrator does not resign willingly from his position or the contracting parties have not reached an agreement. No appeal shall lie from the decision rendered by the court.

3/ The resignation of an arbitrator from his position or the removal of an arbitrator by agreement of the contracting parties in accordance with Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall not be deemed as arbitrator's acceptance of the conditions stated in Sub-Article (1) of this Article.

**17. <u>Appointment of Substitute Arbitrator</u>**

1/ A substitute arbitrator shall be appointed where an arbitrator is removed or resigns from his position as an arbitrator for any reason.

2/ Unless the contracting parties agree on new terms of appointment, a substitute arbitrator shall be appointed in accordance with the same procedure that was applicable to the appointment of the replaced arbitrator.

3/ The contracting parties may agree to continue with the arbitration proceeding conducted by the replaced arbitrators from where it stopped or start a new proceeding. Where no agreement has been reached, they may apply to First Instance Court.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፲፰. የግልግል ዳኝነት ማዕከላት**

፩/ የግልግል ዳኝነት ማዕከል በመንግሥት ወይም በግል ሊቋቋም ይችላል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የግልግል ዳኝነት ማዕከላትን ይቆጣጠራል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ የሚቋቋሙበትን መስፈርቶች ያወጣል፤ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፫/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ያሉ የግልግል ዳኝነት ተቋማት እንዳይቀጥሉ አይከለክልም፡፡

**፲፱. ጉባዔው ሥልጣኑን በራሱ መወሰን ስለመቻሉ**

፩/ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖር አለመኖርን ጨምሮ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለኝ ወይም የለኝም በሚለው ላይ ጉባዔው የመወሰን ሥልጣን አለው፤ ለዚህ ዓላማ ሲባል በአንድ ዋና ውል ውስጥ የተካተተ የግልግል ዳኝነት አንቀጽ ከዋናው ውል እንደተለየ እና ራሱን እንደቻለ ውል ይቆጠራል፤ የዋናው ውል ፈራሽ እና ዋጋ የሌለዉ መሆን የግልግል ዳኝነት አንቀጹን ዋጋ እንዲያጣ እና ፈራሽ እንዲሆን አያደርገውም፡፡

፪/ በጉባዔው የሥረ ነገር ሥልጣን ላይ የሚነሳ ተቃውሞ ጉባዔው በፍሬ ነገር ላይ የሚያደርገውን ክርክር ከመስማቱ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ መቅረብ አለበት፤ ተዋዋይ ወገኑ የግልግል ዳኛ በመምረጡ ወይም በሂደቱ በመሳተፉ ይህንን ተቃውሞ ከማቅረብ አይከለክልም፡፡

**18. Arbitration Centers**

1/ An arbitration center may be established by government or private person.

2/ Federal Attorney General shall supervise arbitration centers, issue and renew license and provided for criteria for the establishment of the same.The details shall be determined by Regulation to be issued by the Council of Ministers.

3/ This Proclamation shall not prohibit existing arbitration centers from being operational.

**19. Power of Arbitration Tribunal To Determine On its Jurisdiction**

1/ The tribunal shall have the power to determine the existence or non existence of a valid arbitration agreement between the contracting parties including as to whether it has jurisdiction to hear the case or not. For this purpose, arbitration clause which is included in an agreement shall be deemed to be a separate and independent agreement. The fact that the principal agreement becomes null and void shall not make the arbitration clause null and void.

2/ An objection raised against the material jurisdiction of the tribunal shall be submitted before a hearing on point of substance as a preliminary objection. The appointment of an arbitrator by a contracting party or his participation in the process shall not prohibit him from raising the objection.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፫/ በጉባዔው በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ ከግልግል ጉባዔው ሥልጣን በላይ ነው የሚል ተቃውሞ መቅረብ የሚገባው ከሥልጣን በላይ ነው የተባለው ጉዳይ መኖሩ እንደታወቀ መሆን አለበት፡፡

፬/ ጉባዔው ዘግይቶ የቀረበን የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን ወይም የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን ወሰን የሚመለከት ተቃውሞ መቅረብ ያልቻለበት ምክንያት በቂ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ሊቀበለው ይችላል፡፡

፭/ ጉባዔው በሥልጣኑ ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ ተቃውሞ የሚቀርበው ውሳኔው በተሰጠ በ፩ ወር ጊዜ ውስጥ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ተቃውሞ መቅረቡ ጉባዔው በሂደት ላይ ያለውን የግልግል ዳኝነት ከመቀጠል እና ውሳኔ ከመስጠት አያግደውም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ጊዜያዊ መጠበቂያ እርምጃዎች

### ፳. ጉባዔው ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ለማዘዝ ያለው ሥልጣን

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ተዋዋይ ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት በግልግል ዳኝነት የቀረበውን ጉዳይ የሚመለከቱ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች መውሰድ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ጉባዔው ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ An objection that the case is beyond the material jurisdiction of a tribunal shall be submitted as soon as the existence of such condition is discovered.

4/ The Tribunal may accept a late submission of an objection with regard to the material jurisdiction or the scope of its jurisdiction if it believes that there is sufficient justification for the delay.

5/ An objection against the decision of the tribunal on its jurisdiction shall be submitted to First Instance Court within one month from the date of rendering of such decision.

6/ The submission of objection in accordance with Sub-Article (5) of this Article shall not prevent the tribunal from continuing with the arbitration proceedings and rendering an award.

## SECTION FOUR

## INTERIM MEASURES

### 20. Power of the Aribtral Tribunal to Issue Order Interim Measures

1/ Unless the contracting parties agree otherwise, the tribunal may issue an order interim measure upon request made by one of the contracting parties, where it deems it necessary to take interim measures relating to the subject matter of the dispute under arbitration proceedings.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጥ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ትዕዛዝ የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ለመጠበቅ፣

ለ) የክርክሩ አካል የሆኑ ዕቃዎች በተገቢ ሁኔታ እንዲጠበቁ ለማድረግ፣ በሦስተኛ ወገን ዘንድ እንዲቀመጡ ወይም የሚበላሹ ዕቃዎች እንዲሸጡ ለማድረግ፣

ሐ) የግልግል ውሳኔ ሊያርፍባቸው የሚችሉ ሐብቶች እና ፈንዶች እንዲጠበቁ ለማድረግ፣

መ) ለግልግሉ ምክንያት የሆነው አለመግባባት እስኪወሰን ድረስ የነበረው ሁኔታ እንዲቀጥል ወይም ወደ ነበረበት እንዲመለስ ለማድረግ፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ጉባዔው በራሱ ተነሳሽነት የግልግል ዳኝነቱ ሂደትን ለማደናቀፍ የሚችል ወይም ጉዳት ለማድረስ የተቃረበ ጉዳይን እንዲቆም ለማድረግ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፳፩. ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ ለመስጠት ከግምት የሚገቡ ሁኔታዎች እና ስለመያዣ

፩/ ጉባዔው ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ ለመስጠት ትዕዛዙ ባይሰጥ የማይካስ ጉዳት የሚደርስ ስለመሆኑ እና ትዕዛዙ የሚሰጥበት አካል ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ተመዛዛኝነትን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

2/ The order of interim measures rendered in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall include the following:

a) To preserve relevant evidence;

b) To properly preserve or maintain goods that are part of the dispute; to preserve under the custody of third party or to sell perishable goods;

c) To preserve assets and funds against which an arbitration decision may be given;

d) To allow the continuation of the existing conditions or to restore the status quo pending resolution of the dispute.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the tribunal may, on its own initiative, issue order of injunction to stop anything that may create an obstacle to the arbitration proceeding or bring about imminent damage.

## 21. Conditions for Issuing an Order Interim Measures and Security

1/ The tribunal shall, in order to issue an order of provisional interim measure, consider that irreparable damage is likely to happen if an order is not issued or the impact it may have on the person against whom the order is issued.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፪/ ጉባዔው ትዕዛዙን በሚሠጥበት ጊዜ ለሌላኛው ወገን የመሰማት እድል መስጠት አለበት፡፡

፫/ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀረበው ተከራካሪ ወገን ትዕዛዙ ሊያስከትል የሚችለውን ኪሳራ የሚመጥን ዋስትና እንዲያቀርብ ጉባዔው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፬/ የተሰጠው ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ በወቅቱ በነበረው ሁኔታ ሊሰጥ አይገባውም ነበር ተብሎ ከታመነ ጉባዔው ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ያቀረበውን ወገን ከጊዜያዊ ትዕዛዙ ጋር በተያያዘ ለደረሰ ጉዳት ካሣ እንዲከፍል በተጨማሪነት ሊያዝ ይችላል፡፡

## ፳፪. የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ስለመጠየቅ

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር፣ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ትዕዛዝ እንዲሰጡለት ጥያቄ ያቀረበ ተዋዋይ ወገን ሌላኛውን ወገን ሳያሳውቅ በተጓዳኝ የመጠበቂያ እርምጃዎችን ተግባራዊነት እንዳያደናቅፍ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጉባዔውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪/ ጉባዔው ለሌላኛው ወገን ማሳወቁ ትዕዛዙ እንዳይፈፀም ያደርጋል ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲያምን ሌላኛውን ወገን ሳያሳውቅ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዙን ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ The tribunal shall provide the other party an opportunity to be heard while rendering its decision.

3/ The contracting party who has requested the tribunal for an order of provisional interim measure may be required by the tribunal to provide sufficient security to cover the damage that may be caused by the order.

4/ The contracting party who has requested for an order of provisional interim measure may be liable for compensation in relation to damage caused by the interim measure if it is believed that the measure should not have been granted under the circumstance then prevailing.

## 22. Request for an Order of Precautionary Measure

1/ Unless the parties agree otherwise, a party who requested for an order interim measure without notifying the other contracting party may concurrently request the tribunal for an order of precautionary measure to be taken to prevent the latter from obstructing the implementation of the interim measure requested.

2/ The tribunal may issue the order precautionary measure without notifying the other party if it believes with sufficient cause that such notification would hinder the implementation of the interim measure.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፫/ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዙ የተሰጠበት ሌላኛው ወገን ስለጉዳዩ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ጉባኤው እድል ይሰጠዋል፡፡

፬/ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ የሚቆየው ትዕዛዙ ከተሰጠበት እለት አንስቶ ለተከታታይ ፴ ቀናት ብቻ ይሆናል፤ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ጉባኤው የሰጠውን የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ ሌላኛውን ወገን ከሠማ በኋላ ትዕዛዙን ሊያሻሽል፣ ሊያፀና ወይም ሊሽር ይችላል፡፡

፭/ ጉባኤው የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት የጠየቀ ወገን ትዕዛዙ በመሰጠቱ ለሚደርስ ጉዳት ማስያዣ እንዲያሲዝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፮/ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ ወይም ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ መሰጠቱ አግባብ እንዳልነበረ በተረጋገጠ ጊዜ ትዕዛዙ በመሰጠቱ የደረሰ ጉዳት ካለ ትዕዛዙ እንዲሰጥለት ያመለከተ ወገን ኃላፊ ይሆናል፡፡

**፳፫. ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዞችን ስለማሻሻል፣ ለጊዜው ስለማገድ እና መሰረዝ**

ጉባዔው በተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ወይም በልዩ ሁኔታ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ለተዋዋይ ወገኖች በማሳወቅ በራሱ ተነሳሽነት የሰጠውን ትዕዛዝ ለጊዜው ሊያሻሽል፣ ሊያግድ፣ ወይም ሊሰርዘው ይችላል፡፡

3/ The Tribunal may give the other party against whom the order of precautionary measure issued an opportunity to respond on the subject matter.

4/ The duration of the order of precautionary measure shall be only for 30 consecutive days starting from the date of such order rendered. The tribunal may modify, confirm or reverse the order of precautionary measure issued by it in accordance with Sub-Article (2) of this Article where the other party has been informed of such order.

5/ The tribunal may order the party who requested the order of precautionary measure to provide security for the damage that may be caused by such order.

6/ The party who requested the order of precautionary or interim measure shall be responsible for the damage caused by the order where it is proved that the order was not appropriate.

**23. Modification, Temporary Suspension and Reversal of Interim Measures**

The tribunal may, on its own initiative, modify, suspend and reverse the order upon request by the contracting parties or in exceptional circumstances, upon prior notice to the parties.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



**፳፬. <u>ስለማሳወቅ</u>**

፩/ ከተሠጠው የቅድመ ጥንቃቄ ወይም ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ ጋር ተያይዞ የተደረጉ ለውጦች ሲኖሩ ተዋዋይ ወገን ወዲያውኑ ለጉባዔው እንዲያሳውቅ ጉባዔው ሊያዝ ይችላል፡፡

፪/ ቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጥያቄ ያቀረበ ተዋዋይ ወገን ሌላኛው ወገን ቀርቦ እስኪያስረዳ ድረስ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዞችን ለመስጠት ወይም ለማስቀጠል መነሻ የሆኑ የማናቸውንም ሁኔታዎች ለውጥን ለጉባዔው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

**24. <u>Notification</u>**

1/ The tribunal may order the contracting party to promptly notify it if there is any change in relation to the order of precautionary or interim measure.

2/ The contracting party who has requested for an order of precautionary measure shall notify the tribunal any change of conditions that have been the causes for issuing an order of precautionary measure or extension of the same until the other contracting party provides his defense at the tribunal.

**፳፭. <u>ለጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እውቅና ስለመስጠት እና ስለማስፈጸም</u>**

፩/ የውጭ ፍርዶችን እውቅና ስለመስጠት እና አፈጻጸምን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተሰጠበትን ሀገር ከግምት ሳያስገባ በጉባዔ የተሰጠ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

፪/ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ መፈፀም ካልቻለ አንደኛው ወገን ትዕዛዙ እንዲፈፀምለት ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ጥያቄ የቀረበው ከሀገር ውስጥ ከሆነ፣ ጉዳዩ ለግልግል ዳኝነት ባይቀርብ ኖሮ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቀርባል፣ ትዕዛዙ በውጭ ሀገር በሚገኝ የግልግል ዳኝነት የተሠጠ ከሆነ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

**25. <u>Recognition and Enforcement of an Order of Interim Measure</u>**

1/ Without prejudice to recognition and enforcement of foreign awards, an order of interim measure issued by a tribunal shall be binding, irrespective of the country in which it was issued.

2/ Where an order for interim measure cannot be enforced, one of the contracting parties may apply to a court for the enforcement of such order.

3/ Where the application made pursuant to Sub-Article (2) of this Article is from within the country, it shall be submitted to a court which would have had jurisdiction had it not been submitted to the tribunal. Where the order is issued by a foreign tribunal, the Federal High Court shall have jurisdiction over the case.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉባዔው በዋስትና ላይ ባልወሰነ ጊዜ እና ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲፈጸምለት የሚጠይቀውን ወገን ወይም የሦስተኛ ወገኖችን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፤ የቀረበው ጥያቄ ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡

፭/ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲፈጸምለት ለፍርድ ቤት ያቀረበ ተዋዋይ ወገን በጉባዔው የተሰጠውን ትዕዛዝ አስመልክቶ የተደረገ ማንኛውንም መሻሻል፣ ጊዜያዊ እግድ ወይም መሰረዝ ለፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፳፮. <u>ጊዜያዊ የመጠበቂያ የእርምጃ ትዕዛዝ እውቅና እንዲሰጥ ወይም እንዲፈፀም የቀረበ ጥያቄን በፍርድ ቤት ስላለመቀበል</u>**

፩/ ፍርድ ቤት ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዞችን በተመለከተ እውቅና እንዲሰጥ ወይም እንዲፈጸም የቀረበውን ጥያቄ የሚከተሉትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ላለመቀበል ይችላል፡-

ሀ) ፍርድን ላለመቀበል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ የተዋዋይ ወገን ችሎታ ማጣት፣ የፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት አለመኖርን፣ ለትዕዛዝ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በግልግል ዳኝነት የማይታይ ከሆነ ወይም ጉባዔው ሥልጣን የሌለው ከሆነ ወይም ትዕዛዙ ጉባዔው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ ከሆነ፣

4/ The court to which a request has been made as provided in Sub-Article (3) of this Article shall order the contracting party to provide security where no decision has been given by the tribunal concerning security and where it finds it necessary to protect the interest of the party who has requested for the enforcement of the interim order or third parties. The request made shall be served on the other contracting party.

5/ The contracting party who has requested for the enforcement of interim measure shall inform the court promptly of any modification, temporary suspension or reversal of the interim measure.

**26. <u>Refusal of the Request for Recognition or Enforcement of Interim Measure by the Court</u>**

1/ A court may refuse the request for recognition or enforcement of an order interim measures on the following grounds:

a) Where the provisions with respect to refusal of award, in particular, loss of capacity of contracting party, absence of a valid arbitration agreement, where the subject matter of the order is not subject to arbitral submission or the tribunal has no jurisdiction or the order is beyond the scope of the tribunal;

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


ለ) መያዣን አስመልክቶ በጉባዔው የተሰጠው ውሳኔ ያልተከበረ እንደሆነ፣

ሐ) ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ የተሻሻለ፣ በጊዜያዊነት የታገደ ወይም የተሰረዘ እንደሆነ፣

መ) ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የሌለው ሆኖ ሲያገኘው፣ ወይም

ሠ) የጊዜያዊ መጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዙን መቀበል ወይም ማስፈጸም ከሕዝብ ሞራልና ፖሊሲ ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲያገኘው፡፡

፪/ ትዕዛዙ እንዲፈፀምለት የቀረበበት ፍርድ ቤት ከላይ የተመለከቱትን ምክንያቶች በመወሰን ሂደት የጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዞቹን ይዘት መከለስ አይችልም፡፡

**፳፯. በፍርድ ቤት ስለሚሰጡ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች**

የግልግል ዳኝነት መቀመጫው በየትኛውም ቦታ ያደረገ የግልግል ዳኝነት ከግምት ሳይገባ ተዋዋይ ወገኖች የጊዜያዊ መጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው ፍርድ ቤትን ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ግልግል ዳኝነት ሂደት

**፳፰. ተዋዋይ ወገኖችን በእኩልነት ስለመስማት**

የግልግል ዳኝነቱ ሁሉም ተዋዋይ ወገኖች እኩል የመስተናገድ፣ ጉዳያቸውን የማቅረብ እና የመሰማት መብት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

b) Where the decision of the tribunal with respect to security has not been complied with;

c) Where the decision rendered with respect to interim measure has been modified, temporarily suspended or reversed;

d) Where the court has no jurisdiction; or

e) Where the recognition or enforcement of the interim measure conflict with public morality or Government Policy.

2/ The court, before which a request has been made, as regard to the above grounds, may not revise the substance of the interim measure in the process of rendering decision.

**27. Interim Measures Granted by Court**

Contracting parties may request a court for an order of interim measure irrespective of the place of the arbitration of the arbitral tribunal.

## SECTION FIVE

## PROCEEDINGS OF ARBITRATION

**28. Equal Treatment of Parties**

Parties to the arbitration agreement shall be treated equally and shall be given the opportunity to present their cases and shall have the right to be heard.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



**፳፱. ሥነ- ሥርዓትን ስለመወሰን**

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተዋዋይ ወገኖች ጉባዔው ሊከተለው የሚገባውን ሥነ-ሥርዓት በስምምነት ሊወስኑ ወይም በሦስተኛ ወገን እንዲወሰን ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በስምምነት የተወሰነ ሥነ-ሥርዓት ከሌለ ጉባዔው ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውን ሥነ-ሥርዓት ይወስናል፣ ሥነ-ሥርዓትን ስለመወሰን ለጉባዔው የተሰጠው ሥልጣን የማስረጃ ተቀባይነት፣አስፈላጊነት እና ምዘናን የተመለከቱ ጉዳዮችን ይጨምራል፡፡

**፴. የጉባዔው መቀመጫ ቦታ**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚካሄድበትን በሕግ አግባብ የግልግል ዳኝነት መቀመጫ ተብሎ የሚጠራውን ቦታ በስምምነት መምረጥ ይችላሉ፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት የሚካሄድበትን ቦታ በስምምነት መምረጥ ካልቻሉ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን መቀመጫ መወሰን አለበት፡፡

፫/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር፣የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ቢኖሩም፣ ለምክክር፣ የምስክርን ቃል ለመስማት፣ የባለሙያዎችን ቃል ለመቀበል፣ ንብረቶችንና ሰነዶችን ለመመርመር ወይም ተያያዥ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን የግልግል ዳኝነት ጉባዔው እንደ አስፈላጊነቱ በሌላ ቦታ ሊያከናውን ይችላል፡፡

**29. Determination of Rules of Procedure**

1/ Without prejudice to the mandatory provisions of this Proclamation, contracting parties may, by agreement, determine the rules of procedure to be applicable by the tribunal or refer to third party for determination.

2/ Where there are no rules of procedure determined in accordance with Sub-Article (1) of this Article, the tribunal shall determine rules of procedure which it deems appropriate. The Power conferred on the arbitral tribunal to determine the rules of procedure includes matters relating to admissibility, relevance and evaluation of evidence.

**30. Place of the Arbitration Tribunal**

1/ The contracting parties may determine by agreement the place of the arbitration that is designated as the place of arbitration by law.

2/ If the contracting parties fail to agree on the place of arbitration, the arbitral tribunal shall determine the place appropriate for the case.

3/ Notwithstanding Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the arbitration tribunal may, unless otherwise agreed by the contracting parties, conduct the arbitration in another place, as may be necessary, for the purpose of consultation, hearing witnesses, receiving testimony of experts, and inspecting property and documents.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፴፩. የግልግል ዳኝነት ሂደት ስለመጀመርና ስለማሳወቅ**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የተጀመረበት ቀን ተብሎ የሚታሰበው ከሳሽ ክርክሩን ለግልግል ዳኝነት ለመምራት እንደወሰነ የሚገልፅ ጥያቄ ለተከሳሽ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ነው፤ የግልግል ዳኝነት ጥያቄው በጽሁፍ ሆኖ የተዋዋይ ወገኖችን ሥም፣ ለግልግል ዳኝነት ምክንያት የሆነውን አለመግባባት እና መነሻ የሆነውን የግልግል ስምምነት አንቀጽ የሚያጣቅስ መሆን አለበት፡፡

፪/ የግልግል ዳኝነት ጥያቄው የደረሰው ተዋዋይ ወገን የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖር አለመኖሩን፣ስለ አለመግባባቱ፣ በግልግል ዳኝነት ለመቀጠል ያለውን ፍላጎት በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሹን ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ የግልግል ዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት ተዋዋይ ወገን የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖሩን ከካደ፣ በግልግል ዳኝነት ለመቀጠል ፍላጎት የሌለው መሆኑን ከገለፀ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ ካልሰጠ ጥያቄ አቅራቢው ወገን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

፬/ ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት ሰው ወይም በጠበቃ መወከል ይችላሉ፤ የግልግል ዳኝነት ሂደትን በወኪል ማከናወን የፈለገ ወገን የሚወክለውን ሰው ሥምና አድራሻ የያዘ ማሳወቂያ ለሌላኛው ወገን እና ለጉባዔው መላክ አለበት፡፡

**31. Commencement and Notification of Arbitral Proceedings**

1/ Unless the parties agree otherwise, the date the defendant receives the plaintiff's request that he has decided to refer the dispute to arbitration shall be deemed to be the commencement date of the arbitral proceedings. The request for arbitration shall be in writing and shall specify the names of the parties, the dispute that gives rise to the arbitration and the arbitration clause for initiating such arbitration.

2/ The party who has received the request for arbitration shall reply in writing within 30 consecutive days whether there is an arbitration agreement or not, about the dispute and his interest to continue with the arbitration.

3/ The requesting party shall have the right to apply to a court where the party to whom a request has been made denies the existence of an arbitration agreement or expresses no interest in continuing with the arbitration or has not replied within the time limit specified in Sub-Article (2) of this Article.

4/ Parties may be represented by a person of their choice or an attorney. A party who intends to be represented at the arbitration proceedings shall send a notice consisting of the name and address of the agent to the other party and the tribunal.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፭/ በተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ የግልግል ዳኝነት የክስ መጥሪያን እና ማንኛውም ማስታወቂያ በሚከተሉት አማራጮች የሚደርስ ይሆናል፦

ሀ) ማንኛውም የጽሁፍ ማስታወቂያ ለተቀባዩ ወይም ለሕጋዊ ወኪሉ በአካል ከተሰጠ፣ በሥራው ወይም በመደበኛ መኖሪያ ቦታው ከደረሰ፣ ተዋዋይ ወገኖች በሚገለገሉበት ወይም በግልግል ዳኝነት ስምምነታቸው ወይም በዋናው ውል ውስጥ በተጠቀሰው የኢሜይል አድራሻ የተላከ እንደሆነ ማስታወቂያው እንደደረሰ ይቆጠራል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ለተዋዋይ ወገን ማስታወቂያ ወይም መጥሪያ እንዲደርስ ለማድረግ ተገቢው ጥረት ተደርጎ ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ተዋዋይ ወገን በመጨረሻ ይኖርበት በነበረበው መደበኛ የመኖሪያ ቦታ ወይም ንግዱን በሚያከናውንበት አድራሻ በመላክ ወይም ይጠቀምበት በነበረው የፖስታ፣ ኢሜይል፣ በመልዕክተኛ ከተላከ ወይም ማስታወቂያ ወይም መጥሪያው በጽሁፍ መድረሱን ለማሳየት በሚቻልበት ማናቸውም መንገድ ከተላከ ማስታወቂያ ወይም መጥሪያ እንደደረሰ ይቆጠራል፡፡

ሐ) ተቀባዩ ማስታወቂያውን ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ወይም መድረሱን ለመግለፅ እምቢተኝነቱን የግልግል ጉባዔው ካረጋገጠ ተቀባይ መጥሪያው እንደደረሰው ተቆጥሮ በሌለበት ክርክሩ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

5/ Unless the parties agree otherwise, summon of the arbitration suit and any notice shall be served through the following options:

a) A notice shall be deemed to have been delivered where it has been served on the concerned person or legal representative in person, on work place or principal residence, sent through the email addresses used by the parties or the email addresses mentioned in the main contract;

b) Where a reasonable efforts has been made to serve notice or summon on the party based on the provision of paragraph (a) Sub-Article (5) of this Article and has produced no result, such notice or summon shall be deemed to have been served if it is delivered at his last known principal residence or place of business or if it sent through his postal or email addresses used by him or delivered by courier or by any other means of written communication that shows that the notice or summon has been delivered.

c) The notice or summon shall be deemed to have been served and the suit shall be heard ex-parte if the party was not willing to accept the notice or summon and his refusal is ascertained by the tribunal.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፮/ የጊዜ ገደብን ለማስላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተመለከቱት አማራጮች መሠረት የደረሰ መጥሪያ ወይም ማስታወቂያ ቀን መቁጠር የሚጀመረው መጥሪያው ከደረሰበት ወይም ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀጥሎ ባለው ቀን ይሆናል፡፡

## ፴፪. ቋንቋ

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኝነት ሂደት ስለሚጠቀሙበት ቋንቋ በስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች በቋንቋ ምርጫ መስማማት ካልቻሉ ጉባዔው አግባብነት ያለውን ቋንቋ ይወስናል፡፡

፫/ ጉባዔው የሰነድ ማስረጃዎች በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም በጉባዔው ውሳኔ መሠረት በተመረጠው ቋንቋ ወይም በተመረጡት ቋንቋዎች ተተርጉሞ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡

፬/ ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉት የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን የሥራ ቋንቋ ለማይችል ተዋዋይ ወገን፣ ምስክር ወይም ልዩ አዋቂ በሚረዳው ቋንቋ ወይም በምልክት ቋንቋ እንዲተረጎምለት አስተርጓሚ ይመደብለታል፡፡

## ፴፫. ስለ ክስ ማመልከቻ እና የመከላከያ መልስ

፩/ የክስ ማመልከቻ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን ድንጋጌ በማጣቀስ የከሳሽና የተከሳሽ አድራሻን፣ የክሱን አቤቱታና የሚደግፉትን ፍሬ ነገሮች እና ከሳሽ የሚጠይቃቸውን ዳኝነቶች በማካተት ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

6/ The time limit of a notice or summon served with the options provided for in Sub-Article (5) of this Article shall begin to run on the following day after the delivery of the notice or summon.

## 32. Language

1/ Contracting parties may, by agreement, determine the language to be used in the arbitration proceedings.

2/ The arbitral tribunal may determine the appropriate language for the arbitral proceedings where the parties fail to agree on the choice of language.

3/ The arbitral tribunal may order that documentary evidence be submitted accompanied by a translation to the language or languages chosen under the agreement of the parties or the language determined by the tribunal.

4/ Unless the contracting parties agree otherwise, the arbitral tribunal shall,in order to translate to the language he understands or to the sign language, assign a translator to a contracting party, witness or expert who cannot communicate in the working language of the tribunal.

## 33. Statement of Claim and Statement of Defense

1/ The statement of claim shall, by citing the arbitration clause, be submitted with supportive evidence by including the addresses of the plaintiff and the defendant, the claim and material facts supporting his request, the reliefs sought by the plaintiff.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፪/ የክስ ማመልከቻው፡-

ሀ) በተዋዋዮች ስምምነት በተገለፀው ጊዜ ውስጥ፣

ለ) ተዋዋዮች በመረጡት የግልግል ዳኝነት ማዕከል ሥነ-ሥርዓት በተደነገገው ጊዜ ውስጥ፣ወይም

ሐ) የተዋዋዮች ስምምነት በሌለ ጊዜ ጉባዔው በወሰነው ጊዜ ውስጥ፣ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ ተከሳሽ በክስ አቤቱታ የተመለከቱትን ዝርዝር ፍሬ ነገሮች ባካተተ መልኩ መልሱን እና ደጋፊ ማስረጃ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

፬/ መልስ የሚቀርብበት ጊዜ በተዋዋይ ወገኖች ወይም በግልግል ጉባዔው ባልተወሰነ ጊዜ ተከሳሽ ክሱ በደረሰው በ፷ ቀናት ውስጥ መልስ ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ ክስ ወይም መልስ በቀረበበት ጊዜ ማሻሻያውን ያላደረገበት ወይም ማስረጃውን ያላቀረበበት ምክንያት በቂ መሆኑን እና የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የሚገኝበትን ደረጃ ከግምት በማስገባት ጉባዔው ተገቢ አይደለም ብሎ ካልከለከለ በስተቀር ማንኛውም ወገን ክሱን ወይም የክስ መልሱን በግልግል ዳኝነት ሂደት ሊያሻሽል እና ተጨማሪ ማስረጃዎችን ሊያያይዝ ይችላል፡፡

2/ The statement of claim shall be submitted within the period:

a) Stated in the arbitration agreement,

b) Stipulated in the rules of procedure of the arbitration center that the parties have chosen, or

c) Set out by the arbitral tribunal provideded that there is no agreement by the parties.

3/ The defendant shall prepare and submit his statement of defence by including the material facts stated in the statement of claim with the supportive evidence.

4/ Where the time period for submitting a statement of defence is not determined, the defendant shall submit the same within 60 days from the date of receipt of the statement of claim.

5/ Unless the contracting parties agree otherwise, any contracting party may amend his statement of claim or statement of defence and submit additional evidences in the course of the proceeding unless the tribunal considers the reason for not amending the statement or submitting the evidence is sufficient and finds it to be inappropriate by taking into account the stage of the proceeding.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


## ፴፬. የቃልና የጽሁፍ ክርክሮች

፩/ ተከራካሪ ወገኖች ያደረጉት ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቃል ክርክርን የመስማት ወይም ክርክሩን በሰነድ ወይም በሌሎች ግዙፍ ማስረጃዎች ላይ ተመሥርቶ ተገቢውን የማድረግ ሥልጣን የጉባዔው ይሆናል፡፡

፪/ ተከራካሪ ወገኖች የቃል ክርክር ቀሪ እንዲሆን ካልተስማሙ በስተቀር ጉባዔው ስለክርክሩም ሆነ ስለማስረጃ አቀራረብ ከወሰነ በኋላ ለተከራካሪ ወገኖች በቂ የመዘጋጃ ጊዜ መስጠት አለበት፤የቃል ክርክር እንዲደረግ ከጠየቁ ጉባዔው የቃል ክርክሩን በተገቢው ወቅት ማካሄድ አለበት፡፡

፫/ አንዱ ወገን በክርክር ጊዜ ለጉባዔው የሚሰጣቸው መግለጫዎች፣ ሰነዶችና ሌሎች ማስረጃዎች ሁሉ ለሌላ ተከራካሪ ወገንም ወዲያውኑ ሊደርሱት ይገባል፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ጉባዔው ለውሳኔው መሠረት የሚያደርጋቸው የባለሙያ አስተያየቶች ለተከራካሪ ወገኖች ሊደርሱ ይገባል፡፡

## ፴፭. የተከራካሪ ወገን መቅረት

በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፡-

፩/ ከሳሽ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ክሱን ያላቀረበ እንደሆነ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው መዝገቡን ይዘጋዋል፡፡

## 34. Oral and Written Arguments

1/ Without prejudice to the agreement made between the parties in dispute, the power to hear oral litigation and take the necessary actions based on documentary and other material evidence shall be vested on the arbitral tribunal.

2/ Unless the parties in dispute agree to abandon oral litigation, the tribunal shall provide the parties with sufficient time for preparation after having decided on conducting of litigation and submission of evidence. If they request for oral argument, the tribunal shall conduct the same within reasonable period of time.

3/ All statements, documents and other evidence submitted to the tribunal by any of the parties during the proceedings shall also be provided to the other party. Likewise, all expert statements on which the tribunal bases its arbitral award shall be given to the parties in dispute.

## 35. Non-Appearance of a Party in Dispute

Unless the contracting parties agree otherwise:

1/ Where the plaintiff fails to submit the statement of claim in accordance with Sub-Article (1) of Article 33 of this Proclamation, the arbitral tribunal shall dismiss the suit.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፪/ ተከሳሽ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የመከላከያ መልሱን ያላቀረበ እንደሆነ፣ ጉባዔው ተከሳሹ የከሳሽን ክስ እንዳመነ ሳይቆጥር የዳኝነት ሂደቱን ይቀጥላል፡፡

፫/ ክርክር በሚሰማበት ጊዜ ከሳሽ ካልቀረበ እና በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ ካመነ ባመነበት ላይ ጉባዔው ውሳኔ ይሰጣል፤ ተከሳሽ ክሱን ክዶ የተከራከረ እንደሆነ መዝገቡን ይዘጋዋል፡፡

፬/ ማንኛውም ተዋዋይ ወገን በአካል ካልቀረበ ወይም ሰነዶችን ያላቀረበ እንደሆነ ጉባዔው የግልግል ዳኝነት ሂደቱን መቀጠል እና በቀረበለት መረጃ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቢኖርም ተዋዋይ ወገን በአካል ያልቀረበው ወይም ማስረጃዎች ያላቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ጉባዔው ሲረዳ የተካሄዱ ሂደቶች ቀሪ እንዲሆኑ፣ ሂደቱ ወደ ኋላ እንዲመለስ ወይም ማስረጃዎቹን እንዲያቀርብ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፮/ ቀጠሮውን አክብሮ ለመጣው ወገን ጉባዔው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ወጪ እና ኪሳራ ይወስናል፡፡

2/ Where the defendant fails to submit his statement of defence in accordance with the provisions of this Proclamation, the arbitral tribunal shall proceed with the proceedings without considering such event as admission of the pleader's claim.

3/ If a plaintiff fails to appear at the hearing and the defendant admits the claims, the arbitral tribunal may pass decision on such admission and dismiss the case if the defendant denies the claims of the plaintiff.

4/ Where none of the parties appear in person or no document have been submitted, the tribunal may continue the proceeding and make an arbitral award on the basis of the evidence submitted to it.

5/ Notwithstanding the Provision of Sub-Article (4) of this Article, the tribunal may terminate the proceedings, restart the proceedings or allow the submission of evidence if it recognizes that the contracting party has sufficient reason for not appearing in person at the hearing or submitting its evidence.

6/ The tribunal shall award such cost and expenses in accordance with the Civil Procedure Code for the party who has appeared before the tribunal.

## ፴፮. ባለሙያ ስለመሰየም

፩/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ጉባዔው፡-

ሀ) በቃል ወይም በጽሁፍ ሙያዊ ማብራሪያ ሊሰጥ የሚችል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሙያተኛ ሊሰይም ይችላል፣

ለ) ማንኛውም ተዋዋይ ወገን ለሙያተኛው አግባብነት ያለውን መረጃ እንዲሰጥ ወይም ሙያተኛው አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች፣ ዕቃዎች ወይም ሌሎች ንብረቶች እንዲፈትሽ ወይም እንዲመረምር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር መጠየቅ ይችላል፡፡

፪/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ በተዋዋይ ወገኖች በሚቀርብ ጥያቄ ወይም ጉባዔው በራሱ ተነሳሽነት ሙያተኛ መቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሙያተኛው ሙያዊ ማብራሪያውን በጽሁፍ፣ በቃል ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ለጉባዔው ካቀረበ በኋላ በዳኝነት ሂደቱ ላይ ተገኝቶ በተዋዋይ ወገኖች ለሚቀርብለት ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጥ በጉባዔው ሊታዘዝ ይችላል፡፡

፫/ የቀረበውን የሙያ ምስክር በሚሰጠው ምስክርነት ላይ ሙያዊ ብቃቱን፣ ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን ተዋዋይ ወገን ለመቃወም ይችላል፡፡

## 36. Assignment of Expert

1/ Unless the contracting parties agree otherwise, the arbitral tribunal may:

a) Assign one or more expert who can provide expert opinion orally or in writing;

b) Request any contracting party to provide relevant information to the expert, or to create conducive environment for the expert to inspect and examine relevant documents, objects and other property.

2/ Unless the contracting parties agree otherwise, the expert may, upon the request of the contracting parties, or where the tribunal finds the appearance of the expert necessary, on its own initiative, order the expert to present his expert opinion in writing, orally or by any other means to provide responses to questions raised by contracting parties by appearing in person at the tribunal.

3/ The contracting party may challenge the professional competence, impartiality and independence of the expert with respect to his expert opinion.

**፴፯. ማስረጃን ለመቀበል በፍርድ ቤት የሚደረግ ድጋፍ**

፩/ ጉባዔው በራሱ ወይም አንዱ ተከራካሪ ወገን የሚያቀርብለትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ፣ ማስረጃዎችን መቀበልና ሌሎች የጉባዔውን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ጉባዔው በራሱ ሥልጣን ሊፈፅማቸው የማይቻሉ ከሆነ ወይም መፈፀም ካልቻለ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት አማካኝነት እንዲፈፀምለት ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሕግን መሠረት በማድረግ ጥያቄውን ውድቅ ካላደረገው በስተቀር ማስረጃውን ይሰማል ወይም እንዲሰማ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ ውጤቱንም በጽሁፍ ለጉባዔው ያሳውቃል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ፍርድ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ጉባዔው እና ተዋዋይ ወገኖች ማስረጃዎቹን በመስማት ሂደት እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**፴፰. የጉዳዩን ሂደት በጽሁፍ ስለማስፈር**

፩/ ጉባዔው የዳኝነት ሂደቱን በጽሁፍ ማስፈር አለበት፤ ተከራካሪ ወገኖች ወይም የግልግል ሂደቱ ተሳታፊዎች ሀሳባቸው ተሟልቶ ካልተጻፈ ወይም ስህተት ያለበት መሆኑን ካመኑ እንዲስተካከል መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**37. Support of Court in Receiving Evidence**

1/ The arbitral tribunal may, upon its own initiative or based on the request of the contracting party, request the assistance of the court that has material jurisdiction over the case in receiving evidence and executing its order where such matter does not fall within its competence or cannot be executed by itself.

2/ The court to which a request has been made in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall, unless the court dismiss the request in accordance with the law, hear evidence or give order for the hearing of same and notify the arbitral tribunal, in writing, about the results.

3/ The court may allow the tribunal and the contracting parties to participate in a hearing to be conducted in accordance with Sub-Article (2) of this Article, as may be necessary.

**38. Recording of the Proceedings in Writing**

1/ The tribunal shall reduce the arbitration proceedings in writing. The parties in dispute or participants of the proceedings may request corrections to be made where their statements are not fully captured or if they believe that there are errors.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፪/ የቀረበው የማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘቱ በመዝገብ መስፈር አለበት፡፡

፫/ መዝገቡ በግልግል ዳኞች በየገፁ መፈረም እና ማህተም መደረግ አለበት፤ ሆኖም የግልግል ዳኝነት ጉባዔ በጊዜያዊነት ከተቋቋመ እና የራሱ ማህተም ከሌለው የግልግል ዳኞች ፊርማ በቂ ይሆናል፡፡

**፴፱. ምስጢራዊነት**

በሕግ ወይም በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የጉባዔው የሥራ ሂደት እና ውሳኔ ምስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፡፡

**፵. የሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት እና ተጠሪነት**

፩/ በግልግል ዳኝነት ውሳኔው ጥቅማቸው ሊነካ የሚችሉ ሦስተኛ ወገኖች ከውሳኔ በፊት አቤቱታቸውን ለጉባዔው በማቅረብ ወደ ግልግል ዳኝነት ሂደቱ መግባት ይችላሉ፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች ለኃላፊነታቸው ሦስተኛ ወገን እንዲጠየቅላቸው ወይም ካሣ እንዲከፍላቸው በማሰብ ሦስተኛ ወገኖች በሂደቱ እንዲገቡ ለጉባዔው ማመልከት ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ሦስተኛ ወገኖች ወደ ሂደቱ መቀላቀል የሚችሉት ሦስተኛ ወገኖችን ጨምሮ ተዋዋይ ወገኖችም ፍቃደኝነታቸውን ሲገልጹ ብቻ ይሆናል፡፡

2/ The acceptance or rejection of the request for correction shall be stated in the file.

3/ The arbitrators shall put their signature on each page of the file and a seal shall be affixed thereto. However, where an ad hoc arbitration panel is established and if such panel does not have its own seal, the signature of the arbitrators shall suffice.

**39. Confidentiality**

Unless otherwise provided by law or agreement, the proceedings and arbitral award of the tribunal shall be kept confidential.

**40. Intervention of Third Parties and Accountability**

1/ Any third party whose interest could be affected by the arbitral award may intervene in the arbitral proceedings before the arbitral award is rendered upon submission of their application to the tribunal.

2/ The contracting parties may apply to the tribunal for the intervention of third parties in the proceedings with the intention of holding the latter liable to them or requiring such parties to pay them compensation.

3/ Third parties may only participate in the proceedings if the contracting parties including the third party give their consent to such intervention.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


## ክፍል ስድስት

## የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እና የሂደቱ መቋረጥ

### ፵፩. በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ መሠረታዊ ሕጎች

፩/ ዓለም አቀፍ በሆኑ የግልግል ዳኝነት ጉዳዮች ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተፈፃሚ እንዲሆን የመረጡትን መሠረታዊ ሕግ ጉባዔው የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በተዋዋይ ወገኖች የሚደረግ የትኛውም የሕግ ምርጫ ስምምነት ከጉዳዩ ጋር የተገናኘውን የሌላ ሀገር መሠረታዊ ሕግ የሚመለከት እንጂ የግጭት ሕግ እንዳልሆነ ይገመታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በስምምነት የተመረጠ ሕግ ከሌለ ጉባዔው ከጉዳዩ ጋር ቅርበትና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በመምረጥ ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

፬/ ጉዳዩ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ይዘት የሌለው ከሆነ ጉባዔው የኢትዮጵያን ሕግ ብቻ ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

፭/ በርትዕ ወይም የታወቁ የንግድ ልምዶችን መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው ተዋዋይ ወገኖች ለጉባዔው ይህንን ዓይነት ሥልጣን በግልጽ ከሰጡ ወይም ተፈፃሚው ሕግ ይህን ለማድረግ ሥልጣን የሚሰጠው ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## SECTION SIX

## ARBITRAL AWARD AND TERMINATION OF THE PROCEEDINGS

### 41. Applicable Laws on the Subject Matter of the Case

1/ The arbitration tribunal shall have the obligation to apply the substantive law chosen by the contracting parties to international arbitration.

2/ Unless specifically agreed otherwise, any choice of law made by agreement of the parties shall be deemed to be the substantive law of that country and not that of the conflict of laws rules.

3/ Where no substantive law has been chosen by agreement in accordance with Sub-Article (1) of this Article, the tribunal may choose a substantive law close and relevant to the subject matter of the dispute.

4/ Where the subject matter of the dispute does not have an element of international arbitration, Ethiopian law shall apply.

5/ An arbitral award may be granted based on equity or known commercial practices where such power is expressly given to the tribunal by the contracting parties or the applicable law authorizes such application.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፵፪. ከአንድ በላይ በሆኑ የግልግል ዳኞች ስለሚሰጥ ውሳኔ**

፩/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ የግልግል ዳኞች የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ የሚሰጠው በድምፅ ብልጫ ነው፤ በልዩነት የተሰጠ ሀሳብ ቢኖር ልዩነቱ ይመዘገባል፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር፣ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ከግልግል ዳኞቹ መካከል በግልግል ውሳኔው ላይ ድምፅ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም የግልግል ዳኛ ይህንኑ ለተዋዋይ ወገኖች በማሳወቅ የተቀሩት የግልግል ዳኞች ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡

፫/ በተዋዋይ ወገኖች ወይም በቀሪዎቹ የግልግል ዳኞች ሥልጣን የተሰጠው የግልግል ዳኛ ሥነ-ሥርዓታዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ጉባዔው ሳይሟላ ትዕዛዞችን ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፵፫. በስምምነት መሠረት ስለሚሰጥ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ**

፩/ በግልግል ዳኝነት በተያዘው ጉዳይ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ በሚደርሱት ስምምነት አለመግባባታቸው የተፈታ እንደሆነ የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ይቋረጣል፡፡

**42. Arbitral Award Rendered by More Than One Arbitrator**

1/ Unless the contracting parties agree otherwise, decision shall be rendered by majority vote where the number of arbitrators is more than one. Dissenting opinion shall be recorded.

2/ Unless the contracting parties agree otherwise, where one of the arbitrators is not willing to cast his vote on the decision, he shall notify the contracting parties and the rest of the arbitrators shall render decision.

3/ An arbitrator may pass decisions on procedural matters with respect to powers given to him by contracting parties or other arbitrators even where the quorum is not present.

**43. Arbitral Award Rendered on the Basis of an Agreement**

1/ The arbitral proceedings shall be terminated where the contracting parties have resolved their dispute by agreement before an arbitral award is rendered on the subject matter of the arbitration.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተዋዋይ ወገኖች የደረሱበት ስምምነት በጉባዔው እንዲመዘገብላቸው ጥያቄ ካቀረቡ እና ውሳኔው የሕዝብን ሞራልና ፀጥታ የማይቃረን ከሆነ አለመግባባቱ የተፈታበት ጉዳይ እንደ ግልግል ጉባዔው ውሳኔ ተቆጥሮ በግልግል ጉባዔው መዝገብ ላይ ሊመዘገብ ይችላል፤ውሳኔው በተያዘው ጉዳይ ላይ እንደ ማንኛውም በጉባዔ የተሰጠ ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡

## ፵፬. የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ፎርም፣ ይዘት እና ውጤት

፩/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በጽሁፍ ሆኖ በግልግል ዳኛው ወይም በግልግል ዳኞቹ መፈረም አለበት፤ከሁለት በላይ የሆኑ የግልግል ዳኞች በተሰየሙበት የግልግል ጉባዔ የሚሰጥ ውሳኔ በአብላጫው ዳኞች መፈረሙ በቂ ሆኖ ያልፈረመ ዳኛ ቢኖር ምክንያቱ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች ምክንያቱ እንዳይገለጽ ያደረጉት ስምምነት ከሌለ በስተቀር ወይም ውሳኔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፫ መሠረት በጋራ መግባባት ላይ ተመሥርቶ የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ምክንያት በግልግል ዳኝነት ጉባዔ መዝገብ መስፈር ይኖርበታል፡፡

2/ Where the contracting parties request the tribunal to register their agreement in accordance with Sub-Article (1) of this Article and if such agreement does not contradict with public morality and security, the matter resolved by agreement shall be deemed to be an award of the tribunal and registered in the tribunal's registry and shall have the same legal effect as any award granted by the tribunal.

## 44. Form, Content and Effect of Arbitral Award

1/ The arbitral award shall be in writing and signed by the arbitrator or arbitrators. Where an arbitral award is rendered by a tribunal with more than two arbitrators, the signature of the majority shall suffice and the arbitrator who has not signed on the arbitral shall state his reasoning.

2/ Unless there is an agreement between the contracting parties not to disclose the reason or the arbitral award is granted based on mutual consent as provided in Article 43 of this Proclamation, the grounds of the award shall be recorded in the file of the tribunal.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፫/ ውሳኔው የግልግል ዳኝነት ጥያቄውን፣ የአለመግባባቱን ፍሬ ነገር፣ የተዋዋይ ወገኖችን ሥም፣ የዳኞቹን ሥም፣ አድራሻ እና እንደ አስፈላጊነቱ ዜግነት፣ ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ምክንያት፣ የግልግል የዳኝነቱን ወጪ አከፋፈል፣ ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ በተደነገገው መሠረት የግልግል ጉባኤው መቀመጫ ቦታን መግለጽ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በግልግል ዳኞች የተፈረመ የውሳኔ ግልባጭ ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን ውሳኔው በተፈረመ በ፲፭ ቀናት ውስጥ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም፣ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የዳኝነቱን ሙሉ ክፍያ እና ወጪ በውሳኔው መሠረት እስኪከፈል ድረስ የውሳኔውን ግልባጭ ላልከፈለው ተዋዋይ ወገን እንዲሰጥ አይገደድም፡፡

፮/ ማንኛውም የግልግል ዳኝነት ጉባዔ የሚሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤት እንደተሰጠ ፍርድ ይቆጠራል፣ በተዋዋይ ወገኖች ላይ አስገዳጅ እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ክስ ከማቅረብ ይከለክላል፡፡

## ፵፭. የግልግል ዳኝነትን ሂደትን ስለማቋረጥ

፩/ የግልግል ዳኝነት ሂደት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

ሀ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔ መሰጠቱ ለተከሳሽ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ክስ አቅራቢው ክሱን ሲያነሳ፣

3/ The award shall state the claim, the material facts in dispute, the name, address and, where necessary, the Citizenship of the contracting parties, grounds for rendering the award, the costs of and mode of payment of costs of arbitration, the date of the award, and place of the arbitral award as stipulated under Article 30 of this Proclamation.

4/ A copy of the award duly signed by the arbitrators in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be provided to each contracting party within 15 days from the date of signing of the award.

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) of this Article, the tribunal shall not be compelled to issue a copy of the award to a contracting party who fails to settle payment until the arbitration fee and costs are fully paid as provided for in the award.

6/ Any decision of the arbitral tribunal shall be deemed to be a decision given by a court and shall be binding on the parties and prevents from bringing suit on similar matter between such parties.

## 45. Termination of Arbitration Proceedings

1/ Arbitration proceedings shall terminate on the following grounds:

a) Where the plaintiff withdraws his suit and the granting of the award will not be in the interest of the defendant;

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


ለ) ተዋዋይ ወገኖች ዳኝነቱ እንዲቋረጥ ሲስማሙ፣

ሐ) የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የዳኝነት ሂደቱን ማስቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው ወይም ሂደቱን ለማስቀጠል የማያስችል በቂ ሁኔታ ሲኖር፣

መ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ሲሰጥ፣ወይም

ሠ) በሌሎች ሕጎች በግልፅ በተደነገጉ በማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የግልግል ዳኝነቱ ሲቋረጥ ወጭውን በሚመለከት ጉባዔው ይወስናል፡፡

**፵፮. <u>የግልግል ዳኝነት ወጭ</u>**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ለግልግል ዳኝነት የሚያስፈልገውን ወጪ እና የግልግል ዳኞች አገልግሎት ክፍያን ጨምሮ ጉባዔው በወጭው አከፋፈል ላይ ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በጉባዔው የተሰጠ ውሳኔ ላይ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል፡፡

**፵፯. <u>የግልግል ጉባኤ ውሳኔን ስለማረም፣ መተርጎም እና ስለ ተጨማሪ ውሳኔ</u>**

፩/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ አንድ ተከራካሪ ወገን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ፡-

b) Where the parties agree to terminate the arbitration proceedings;

c) Where the arbitral tribunal finds the continuation of the proceedings unnecessary or there is sufficient reason for not continuing the proceedings;

d) Where an arbitral award is rendered;

e) On any other grounds expressly provided for in other laws;

2/ When the arbitral proceedings are terminated in accordance with Sub-Article (1) of this Article, the tribunal shall pass decision regarding the cost of arbitration.

**46. <u>Costs of Arbitration</u>**

1/ Unless the contracting parties agree otherwise, the modes of payment of costs necessary for the arbitration and service fees of arbitrators may be determined by the tribunal.

2/ An appeal may be lodged against a decision rendered by the tribunal in accordance with Sub-Article (1) of this Article to the First Instance Court.

**47. <u>Corrections, Interpretations and Additional Arbitral Award</u>**

1/ Unless the parties agree otherwise,, any party may within 30 days from receipt of the award:

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



ሀ) አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ በግልግል ዳኝነት ጉባዔው ውሳኔ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣ የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ የቃል ስህተት እንዲታረም መጠየቅ ይችላል፡፡

ለ) አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ በተለየ የውሳኔው ጭብጥ ወይም ክፍል ላይ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ትርጉም እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላል፡፡

ሐ) አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ ውሳኔው ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ቀርቦ የተዘለለ የውሳኔው ክፍል ላይ ተጨማሪ ውሳኔ እንዲሰጥለት የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን መጠየቅ ይችላል፡፡

፪/ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ የተቀበለው እንደሆነ ጥያቄውን በተቀበለ በ፴ ቀናት ውስጥ እንደ ጥያቄው አግባብነት ያርማል ወይም ይተረጉማል፤ ጉባዔው ያደረገው ማስተካከያ ወይም የሰጠው ትርጓሜ የውሳኔው አካል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

፫/ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተዘረዘሩት ስህተቶች መኖራቸውን ሲረዳ በራሱ ተነሳሽነት ውሳኔው በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ ማስተካከል ይችላል፡፡

a) request the tribunal for correction of clerical errors, numerical errors, unintended and inadvertent omission of words by notifying the other party;

b) request the tribunal to give an interpretation on specific issue or part of the award by notifying the other party;

c) request the tribunal for additional award on the part of the award that has been omitted by notifying the other party.

2/ Where the arbitral tribunal accepts the request submitted in accordance with paragraph (a) and (b) of Sub-Article (1) of this Article, it shall make the necessary correction or provide interpretation within 30 (thirty) days from the receipt of the request. The correction made or interpretation provided by the tribunal shall be deemed to be part of the award.

3/ Where the arbitral tribunal discovers the errors stated under paragraph (a) of Sub-Article (1) of this Article, it may make correction upon its own initiative within 30 days from the date of rendering of the award.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፬/ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ የተቀበለው እንደሆነ ጥያቄውን በተቀበለ በ፷ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ ውሳኔ ይሰጣል፣ የሚሰጠው ተጨማሪ ውሳኔ የቀድሞው የውሳኔው አካል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

፭/ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማስተካከያ ለማድረግ፣ትርጓሜ ለመስጠት ወይም ተጨማሪ ውሳኔ ለማስተላለፍ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፬) የተመለከተውን ጊዜ ለተጨማሪ ፳ ቀናት ሊያራዝመው ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፬ የተመለከተው ድንጋጌ ማስተካከያ በማድረግ፣ ትርጓሜ በመስጠት ወይም ተጨማሪ ውሳኔ በማስተላለፍ ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## **ክፍል ሰባት**

## **በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች**

### ፵፰. **የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ስለመቃወም**

፩/ በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ውስጥ የክርክር ተሳታፊ መሆን ሲገባው ያልተሳተፈና በተሰጠው የግልግል ዳኝነት ውሳኔ መብቱ የተነካ ተዋዋይ ወገን ወይም ማንኛውም ሦስተኛ ወገን የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን ወይም የውሳኔውን አፈፃፀም በመቃወም ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ባይታይ ኖሮ ነገሩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰጠቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ፷ ቀን ውስጥ መቃወሚያውን ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ Where the arbitral tribunal accepts the request submitted in accordance with paragraph (c) of Sub-Article (1) of this Article, it shall render additional award within 60 days from the date of receipt of the request. The additional award shall be deemed to be part of the previous award.

5/ Where the arbitral tribunal finds it necessary, it may extend the period mentioned in Sub-Articles (2) and (4) of this Article for additional 20 days in order provide interpretation or render additional decision.

6/ The provisions of Article 44 of this Proclamation may be applicable with respect to making of correction, providing interpretation and rendering of additional decision.

## **SECTION SEVEN**

## **OBJECTIONS AGAINST ARBITRAL AWARDS**

### 48. **Objections Raised Against Arbitral Awards**

1/ A contracting party or a third party who should have been party to the arbitration proceeding and whose right has been affected by the arbitral award may, within 60 days from the date he became aware of such award, submit his objection against the arbitral award or the execution of the same to the court which has jurisdiction over the case had it not been submitted to arbitration.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፪/ መቃወሚያውን የሚያቀርበው ሦስተኛ ወገን አስቀድሞ ጉዳዩን ሲመለከተው ለነበረው ጉባዔ አቤቱታውን አቅርቦ በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ጣልቃ ገብቶ ከነበረ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መቃወሚያውን ማቅረብ አይችልም፡፡

፫/ የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢው ከተዋዋይ ወገኖች መካከል ከሆነ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው ማሻሻያ እንዲደረግበት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ወደ ጉባዔው ይመልሰዋል፡፡

፬/ የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢው ሦስተኛ ወገን ከሆነ ፍርድ ቤቱ የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

፭/ ፍርድን እና አፈፃፀምን ስለመቃወም በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ውስጥ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**፵፱. ይግባኝ**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኝነት ስምምነታቸው በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፡፡

፪/ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር የሠበር አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል፡፡

፫/ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ(፭)፣ አንቀጽ ፵፫፣እና አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት በተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት አይቻልም፡፡

2/ Where the third party who submits his objection had previously submitted the same to the tribunal that heard the case and had intervened in the arbitration proceedings; he may not submit his objection in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ Where the person who raised the objection is among the contracting parties, the court shall remand the award to the tribunal for amendment.

4/ Where the person who raised the objection is a third party, the court may reverse or modify, partly or wholly, the arbitral award.

5/ The provisions of the Civil Procedure Code regarding objection to judgement and execution of order shall be applicable in so far as they are consistent with this Proclamation.

**49. <u>Appeal</u>**

1/ Unless the contracting parties agree otherwise in their arbitration agreement, no appeal shall lie to the court from an arbitral award.

2/ Unless there is agreement to the contrary, an application for cassation can be submitted where there is a fundamental or basic error of law.

3/ Notwithstanding any agreement to the contrary, no appeal shall lie from arbitral award rendered in accordance with Sub-Article (5) of Article 41, Article 43 and Sub-Article (2) of Article 44 of this Proclamation.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፬/ በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ታይቶ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው፤ ይግባኙ የሚቀርበውም የግልግል ዳኝነት ውሳኔው ለይግባኝ ባዩ በደረሰ በ፷ ቀናት ውስጥ ነው፡፡

፭/ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ስለይግባኝ አቀራረብ የተመለከቱት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ በሚቀርብ ይግባኝ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የይግባኝ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን ከ፷ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት አግዶ የማቆየት እና በይግባኙ ላይ ተገቢውን የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፶. የግልግል ዳኝነት ውሳኔን ስለመሻር**

፩/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም፣ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ውሳኔው እንዲሻርላቸው ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ባይታይ ኖሮ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፡፡

፪/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ለማሻር አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ በአንዱ ሆኖ፣ ሁኔታው መኖሩን የማስረዳት ሸክሙ ወይም ኃላፊነት የአመልካቹ ይሆናል፡-

4/ An appeal shall lie form arbitral award to the court that has an appellate jurisdiction had the case been heard by regular Court that has jurisdiction over the case. The Memorandum of Appeal shall be filed within 60 days from the date of delivery of the arbitral award to the appellant.

5/ The relevant provisions of the Civil Procedure Code with respect to appeal from judgement shall be applicable to an appeal that lies from arbitral award.

6/ The Court to which an appeal is lodged pursuant to Sub-Article (5) of this Article shall have the power to suspend the arbitral award for a period not exceeding 60 days and to render appropriate decision on the appeal in accordance with the Civil Procedure Code.

**50. Setting Aside an Arbitral Award**

1/ Notwithstanding any agreement to the contrary, contracting parties may apply to the court that has jurisdiction over the case had the case not been submitted to arbitration to have the arbitral award set aside.

2/ An application to have an arbitral award set aside may be lodged on the following grounds and the burden of proof of the existence of the alleged ground rests with the applicant:

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


ሀ) አመልካቹ ላይ ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መሠረት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ለማድረግ የሚያስችለው ችሎታ የሌለው እንደሆነ፤

ለ) የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ በተዋዋዮች በተመረጠው ሕግ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሆነ ወይም ጊዜው ያለፈ እንደሆነ፤

ሐ) አቤቱታ አቅራቢው ግልግል ዳኞች ስለመሾማቸው፣ ስለግልግል ዳኝነት ሂደቱ በቂ ማስታወቂያ ያልተሰጠው መሆኑን ሲያሳይ ወይም በሂደቱ ክርክሩን ለማሰማት አለመቻሉን ሲያስረዳ፤

መ) የግልግል ዳኞች በሂደቱ ገለልተኛነታቸውን ወይም ነፃነታቸውን ጠብቀው ውሳኔ ያልሰጡ ሲሆን ወይም ከተዋዋይ ወገኖች መደለያ በመቀበል ውሳኔ ሰጥተው ከሆነ፤

ሠ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የተሰጠበት ጉዳይ ከግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ወሰን በላይ ሲሆን ወይም ጉባዔው ከተሰጠው ሥልጣን ወሰን በላይ ውሳኔ የሰጠ ከሆነ፤

ረ) የጉባዔው አመሰራረት እና በሂደቱ የተተገበረዉ ሥነ-ሥርዓት ከተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ጋር የሚቃረን እና ውሳኔው ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ከሆነ ነው፡፡

a) The applicant does not have the capacity to conclude an arbitration agreement as provided for in the law in force;

b) The arbitration agreement becomes null and void under the applicable law chosen by the contracting parties or by Ethiopian law or such agreement has expired;

c) The applicant shows that he has not been given proper notice about the appointment of arbitrators, arbitration proceedings or has not been able to present his case during the proceedings;

d) The arbitrators did not make the award by maintaining their impartiality or independence or have delivered the award by receiving bribe;

e) The subject matter of the arbitral award is beyond the scope of the arbitration agreement or the award rendered is beyond jurisdiction the tribunal;

f) The process of establishment of the tribunal and the procedure applicable in the course of the proceedings contradicts with agreement of the contracting parties and has influenced outcome of the award.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፫/ አቤቱታው የሚቀርበው የግልግል ውሳኔው ለአቤት ባዩ በደረሰ በ፴ ቀናት ውስጥ መሆን አለበት፤ ነገር ግን ውሳኔው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ከተፈፀመ በኋላ ለማሻር የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

፬/ ፍርድ ቤቱ የሚከተሉት ምክንያቶች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን ሊሽር ይችላል፡-

ሀ) በግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት ሕግ መሠረት በግልግል ዳኝነት መታየት የማይችል ሲሆን፤

ለ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን እውቅና መስጠት ወይም እንዲፈፀም ማድረግ በሕዝብ ሞራል፣ ፖሊሲ ወይም ፀጥታ ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ፡፡

፭/ የማሻር አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት በአቤቱታው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ከ፷ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ አግዶ ለማቆየት ይችላል፡፡

፮/ ለአቤቱታ መንስዔ የሆነውን ምክንያት ከግምት ውስጥ በማስገባት ፍርድ ቤቱ ውሳኔው በሙሉ ወይም በከፊል ሳይፈጸም ለማቆየት የእግድ ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን መጀመሪያ ወደ ታየበት ጉባዔ ሊመልሰው ይችላል፡፡

፯/ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ካገኘ እና ውሳኔው ሙሉ በሙሉ ከተሻረ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው ዋጋ እንደሌለው ተቆጥሮ ቀሪ ይሆናል፣ የመሻር ውሳኔው በከፊል የሆነ እንደሆነ ቀሪው የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንደፀና ይቀራል፡፡

3/ The application shall be submitted within 30 days from the date of delivery of the arbitral award to the applicant. However, an application to have the award set aside shall not be acceptable if it has been enforced by Ethiopian court.

4/ The court may set aside the arbitral award if the following conditions exist:

a) The matter upon which the award is based is not arbitrable under the Ethiopian arbitration law;

b) The recognition and enforcement of the arbitral award creates problem on public morality, policy or national security;

5/ The court to which an application to set the award aside may suspend the arbitral award for not exceeding 60 days in accordance with the Civil Procedure Code before a decision is made on the application.

6/ The court may, by taking into account the reason for the submission of the application, refer the matter to the tribunal before of which the case was initially heard by suspending the award wholly or partially.

7/ Where the application is accepted and the award is set aside wholly, the arbitral award shall be null and void. Where the award is partly set aside, the part that is not set aside shall remain valid.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፰/ በመሻር አቤቱታው ላይ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

## ክፍል ስምንት

## የግልግል ዳኝነት ውሳኔን እውቅና ስለመስጠትና ስለማስፈጸም

### ፶፩. የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ስለማስፈጸም

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ ወይም ፶፪ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ አስገዳጅ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቢታይ ኖሮ ፍርዱን ሊያስፈፅም ለሚችለው ፍርድ ቤት በማቅረብ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት የፍርድ ውሳኔ በሚፈፀምበት አኳኋን ይፈጸማል፡፡

፪/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲፈፀምለት የሚፈልግ ወገን የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን፣ የውሳኔውን ዋና ቅጅ ወይም ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የውሳኔ ግልባጭ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ ከውጭ ሀገር ለእውቅና ወይም አፈፃፀም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በሚመለከተው አካል የተረጋገጡ ሰነዶች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ቋንቋ ከአፈፃፀም ፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ የተለየ ሲሆን አመልካቹ በፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ አስተርጉሞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8/ No appeal shall lie from the decision rendered by a court on the application.

## SECTION EIGHT

## RECOGNITION AND EXECUTION OF ARBITRAL AWARD

### 51. Execution of Arbitral Awards

1/ Without prejudice to the provisions Articles 50 or 52 of this Proclamation, an arbitral award rendered in Ethiopia or in a foreign country shall be deemed to be binding and shall be executed pursuant to Civil Procedure Code by applying to a court that is empowered to execute the award had the case been heard by a court.

2/ Any party who seeks the execution of arbitral award by a court shall submit the arbitration agreement, the original award or an authenticated copy of the award.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, Arbitral awards brought into Ethiopia for recognition or execution shall be authenticated by the relevant organ.

4/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, where the award is rendered in a language different from the language of the executing court, the applicant shall produce a translation of these documents into the language of the court.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፶፪. <u>የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዳይፈፀም ስለመቃወም</u>**

፩/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዳይፈፀም መቃወም የሚቻለው ከዚህ በፊት ውሳኔው እንዲሻር ለፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦ ውድቅ ያልተደረገ ከሆነ ነው፡፡

፪/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዳይፈፀም መቃወም የሚቻለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው፡-

ሀ) ፍርዱን በተቃወመው ወገን ላይ ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መሠረት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ለማድረግ የሚያስችል ችሎታ ያልነበረው እንደሆነ፣ ወይም የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ እንዲገዛበት በተዋዋዮች በተመረጠው ሕግ መሠረት ወይም የተዋዋዮች ስምምነት ከሌለ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሆነ ወይም ጊዜው ያለፈ እንደሆነ፤

ለ) አቤቱታ አቅራቢው ዳኞች ስለመሾማቸው፣ ስለግልግል ዳኝነት ሂደቱ በቂ ማስታወቂያ ያልተሰጠው መሆኑን ሲያሳይ ወይም በሂደቱ ክርክሩን ለማሰማት አለመቻሉን ሲያስረዳ፤

ሐ) የግልግል ዳኞች በሂደቱ ገለልተኛነታቸውን እና ነፃነታቸውን ጠብቀው ውሳኔ ያልሰጡ ሲሆን ወይም ከተዋዋይ ወገኖች መደለያ በመቀበል ውሳኔ ሰጥተው ከሆነ፤

**52. <u>Objection to Enforcement of Arbitral Award</u>**

1/ An objection to the enforcement of arbitral award may only be made, where an application made to the court previously to have the award set aside has not been dismissed.

2/ An objection to enforcement of arbitral award may only be made on the following grounds:

a) The person who objects to the enforcement was under legal capacity pursuant to the law applicable to him or if the arbitration agreement is null and void under applicable law chosen by the parties or, in the absence of such agreement, under Ethiopian law.

b) The applicant shows that he has not been given proper notice about the appointment of the arbitrator or the arbitral proceedings or has not been able to present his case;

c) The arbitrators did not grant the award by maintaining their impartiality and independence or have delivered the award by receiving bribe;

መ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የተሰጠበት ጉዳይ ከግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ወሰን በላይ ሲሆን፣ ወይም ጉባዔው ከተሰጠው ሥልጣን ወሰን በላይ ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ፤

ሠ) የጉባዔው አመሠራረት እና በሂደቱ የተተገበረው ሥነ-ሥርዓት ከተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ጋር የሚቃረን እና ውሳኔው ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ ከሆነ፤

ረ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የመጨረሻ ውሳኔ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ከሆነ፣ የተሻረ ወይም ውሳኔው የታገደ ከሆነ::

፫/ ፍርድ ቤቱ የሚከተለው ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጥ የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን ሊሽር ይችላል፡-

ሀ) በግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በዚህ አዋጅ መሠረት በግልግል ዳኝነት መታየት የማይችል ሲሆን፤

ለ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን እውቅና መስጠት ወይም እንዲፈፀም ማድረግ በሕዝብ ሞራል፣ ፖሊሲ ወይም ፀጥታ ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ፡፡

፬/ ፍርድ ቤቱ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው እንዲፈፀም ወይም እንዳይፈፀም የፍርድ ባለመብቱ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ የፍርድ ባለዕዳው በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ ትዕዛዝ በመስጠት ነገሩን ለማጣራት ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል፤

d) The subject matter of the arbitral award is beyond the scope of the arbitration agreement or the award rendered is beyond the jurisdiction of the tribunal;

e) The process of establishment of the tribunal and the procedure that has been implemented in the course of the proceedings contradicts with agreement of the contracting parties or the provisions of this Proclamation and has impacted the outcome of the award.

f) The arbitral award has not reached its final stage or is reversed or suspended.

3/ The court may set aside the arbitral award if the following conditions exist:

a) The matter upon which the award is based is not arbitrable under this Proclamation;

b) The recognition or enforcement of the arbitral award create problem on public morality, policy or national security.

4/ Upon request by the arbitral award creditor for the enforcement or non enforcement of the award, the court may make an adjournment to examine the matter by ordering award debtor to produce sufficient security.

፭/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዳይፈፀም የቀረበ ተቃውሞ ላይ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

**፶፫. <u>በውጭ ሀገር ለተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና ስለመስጠት እና አፈፃፀም</u>**

፩/ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚወድቅ ከሆነ በስምምነቱ መሠረት እውቅና ሊሰጠው ወይም ሊፈፀም ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እውቅና ላይሰጠው ወይም ላይፈፀም የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው፡-

ሀ) የእንካ ለእንካ መርህን መሠረት ያላደረገ ሲሆን፤

ለ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በማይፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት መሠረት ወይም ውሳኔው የተሰጠበት ሀገር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ባልተቋቋመ ጉባዔ የተሰጠ እንደሆነ፤

ሐ) የተሰጠው ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊፈፀም የማይችል እንደሆነ፤

መ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞችን ለመምረጥ እኩል መብት ያልነበራቸው እንደሆነ ወይም በክርክሩ ላይ ማስረጃቸውን ለማቅረብ እና ክርክራቸውንም ቀርቦ ለማሰማት እኩል መብት ያልነበራቸው እንደሆነ፤

5/ No appeal shall lie from the decision rendered by a court on the application of non enforcement.

**53. <u>Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards</u>**

1/ Where a foreign arbitral award falls under International Treaties ratified by Ethiopia, it may be recognized or enforced in accordance with such treaties.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, a foreign arbitral award shall not be recognized or enforced only on the following grounds:

a) Where it is not based on reciprocity;

b) Where the arbitral award is based on invalid arbitration agreement or rendered by a tribunal which is not established in accordance with the law of the country in which such award is rendered;

c) The arbitral award rendered cannot be enforced in accordance with Ethiopian law;

d) Where the parties have not had equal rights in appointing the arbitrators or had in presenting their evidence and getting heard in the course of the proceedings;

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



ሠ) ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በኢትዮጵያ ሕግ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የማይችል እንደሆነ፤እና

ረ) የውሳኔውም አፈፃፀም የሕዝብን ሞራል፣ ፖሊሲና ፀጥታ የሚቃረን እንደሆነ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የውሳኔ ይፈፀምልኝ ማመልከቻ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለ ዕርቅ

### ፶፬. አለመግባባትን በዕርቅ ለመፍታት ስለሚደረግ ስምምነት

ተዋዋይ ወገኞች ወደፊት ሊፈጠር የሚችልን አለመግባባት ወይም የተፈጠረውን አለመግባባት በዕርቅ ለመፍታት በጽሁፍ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ስምምነታቸውን ሊገልጹ ይችላሉ፤ይህ ስምምነት ውጤት የሚኖረው በተዋዋይ ወገኖች መካከል ብቻ ነው፡፡

### ፶፭. በጽሁፍ የተደረገ ስምምነት

፩/ አለመግባባትን በዕርቅ ለመጨረስ በጽሁፍ የተደረገ ስምምነት ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ለፍርድ ቤት በሚቀርብ ክስ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት መነሳት የሚችል እና ፍርድ ቤትን ጉዳዩን ከማየት የሚከለክል ይሆናል፡፡

e) Where the matter on which the award is rendered is not arbitrable under Ethiopian law;

f) Where the arbitral award contravenes public policy, moral and security.

3/ An application for the enforcement of arbitral award in accordance with Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall be submitted to Federal High Court.

## SECTION NINE

## CONCILIATION

### 54. Dispute Resolution Through Conciliation Agreement

Contracting parties may express thier agreement, in writing or in any other means, to resolve future or existing dispute through conciliation.This agreement shall only be applicable between the contracting parties.

### 55. Agreement made in Writing

1/ Written agreement made to resolve dispute,as regards the subject matter of the agreement,may be raised as a preliminary objection in the suit brought to the court and bar the court from hearing the case.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፪/ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዕርቅ ለመጨረስ የተደረገው ስምምነት የማይፀና ነው ብሎ ከወሰነ ወይም ዕርቁን ለማድረግ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ውስጥ ያስቀመጡት ጊዜ ያለፈ ከሆነ ወይም ዕርቁን ለመጀመር የማያስችሉ በቂ ምክንያቶች መኖራቸውን ፍርድ ቤቱ ካመነ ክሱን ለመስማት ይችላል፡፡

2/ The court may hear the case brought where it decides that the conciliation agreement is of no effect, or the period for conciliation stated in the agreement has been expired or the court belives that there is no sufficient ground to start the conciliation.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ቢኖርም በጽሁፍ የተደረገ የዕርቅ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ ለማሰጠት ሲባል ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብን አይከለክልም፡፡

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, written conciliation agreement may not bar contracting parties to request, a court that has jurisdiction, an order of interim measures.

## ፶፮. <u>የዕርቅ ሂደት አጀማመር</u>

## 56. <u>Commencement of Conciliation</u>

፩/ እንታረቅ ባይ ወገን ለዕርቁ መነሻ የሆነውን ጉዳይ በመጥቀስና ምላሽ የሚጠብቅበትን ቀን በመወሰን ለሌላኛው ወገን የዕርቅ ሀሳቡን በቃል ወይም በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

1/ The party who initiates conciliation shall notify orally or in writing to the other party his invitation to conciliate by identifying the subject matter of conciliation and determining the date of response.

፪/ የዕርቅ ሀሳቡን ሌላኛው ወገን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቀበሉን የገለፀ እንደሆነ የዕርቅ ሂደቱ ይጀመራል፡፡

2/ The conciliation proceedings shall commence if the other party expresses his acceptance within the period mentioned under Sub-Article (1) of this Article.

፫/ ሌላኛው ወገን ማስታወቂያው በደረሰው በ፴ ቀናት ወይም ምላሽ የሚሰጥበት ቀን እንዳበቃ የዕርቅ ሀሳቡን ለመቀበል እንዳልፈለገ በመቁጠር እንታረቅ ባይ ወገን የዕርቅ ሀሳቡን እንዳነሳ ለሌላኛው ወገን ያሳውቀዋል፡፡

3/ Where the other party does not respond within 30 days from the date of receipt of notification from the other party or upon expiry of the date of response, the party who initiate the conciliation may treat this as a rejection of the invitation to conciliate and shall notify the other party his revocation of the invitation.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፶፯. የአስታራቂዎች ብዛት**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አስታራቂዎች እንዲኖሩ በተለየ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር የዕርቅ ሂደት በአንድ አስታራቂ ይመራል፡፡

፪/ የአስታራቂዎች ቁጥር ከአንድ በላይ የሆነ እንደሆነ አስታራቂዎቹ በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

**57. Number of Conciliators**

1/ Unless the parties agree otherwise to have two or more conciliators, the conciliation proceeding shall be guided by one conciliator.

2/ Where the number of conciliators is more than one, the conciliators shall act jointly.

**፶፰. አስታራቂን ስለመሰየም**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች የተለየ ሥነ-ሥርዓት እንዲኖር ካልተስማሙ በስተቀር፣ በአስታራቂ ብዛት እና ማንነት ላይ ለመስማማት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች አስታራቂ ሆኖ ለመሥራት ተስማሚ የሆነን ሰው እንዲጠቁሟቸው ወይም አስታራቂ በቀጥታ እንዲሰይምላቸው የአንድን ተቋም ወይም የግለሰብ እገዛ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት አስታራቂን ለመጠቆም ወይም ለመሰየም ጥያቄ የቀረበለት ተቋም ወይም ግለሰብ የአስታራቂውን ነፃነት፣ገለልተኛነት እና እንደ አግባብነቱ አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች የተለየ ዜግነት ያለው ስለመሆኑ ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

**58. Appointment of a Conciliator**

1/ Unless the parties agree upon different procedures, they shall strive to agree on the number and identity of conciliators.

2/ Contracting parties may request support from an institution or an individual to nominate a person suitable to act as a conciliator or to directly designate a conciliator.

3/ An institution or individual to whom a request has been made for nominating or appointing a conciliator in accordance with Sub-Article (2) of this Article shall take into consideration the independence, impartiality of the conciliators and, where appropriate, whether the Citizenship of the conciliator is different from that of the contracting parties.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፬/ አስታራቂው ለአስታራቂነት ሲመረጥ ወይም በአስታራቂነት ከተሰየመበት ጊዜ አንስቶ በማስታረቁ ሂደት የሚያጋጥሙትን በነፃነቱ እና በገለልተኛነቱ ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ያሳድራሉ ብሎ የሚገምታቸውን ማናቸውንም አካባቢያዊ ሁኔታዎች ሳይዘገይ ለተዋዋይ ወገኖች መግለጽ ይኖርበታል፡፡

4/ The conciliator shall, upon appointment or at any time thereafter, disclose to contracting parties without delay any circumstances that may arise in the process of conciliation as of the time of his appointment and which he expects may cause reasonable doubt on his independence and impartiality.

## ፶፱. የዕርቅን ጉዳይ ለአስታራቂ ስለማቅረብ

፩/ አስታራቂው እንደተሰየመ ተዋዋይ ወገኖች ስለ ዕርቁ ጉዳይ አጠቃላይ ሁኔታ እና የዕርቁን ፍሬ ነገር በጽሁፍ እንዲያሳውቁት ሊጠይቅ ይችላል፤ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን ለአስታራቂው ያቀረበውን ተጨማሪ የጽሁፍ መግለጫ ቅጂ ለሌላው ወገን እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖችን ጉዳዩን ያጠናክሩልኛል የሚሏቸውን ፍሬ ነገሮች በሰነዶች እና በሌሎች ማስረጃዎች አስደግፈው በተጨማሪነት በጽሁፍ እንዲያቀርቡ አስታራቂው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፫/ አስታራቂው በየትኛውም የዕርቅ ሂደት አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ማንኛውንም ተዋዋይ ወገን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 59. Submission of the Case to the Conciliator

1/ Upon appointment, the conciliator may request the parties to notify him in writing about the overall conditions and material facts of the dispute under conciliation. Each party shall provide the other party with the copy of the supplementary statement that he has submitted to the conciliator.

2/ The conciliator may, in addition, request the parties to submit in writing any facts which strengthen the case with supporting documents or any other evidence.

3/ The conciliator may request any contracting party to submit to him any additional evidence which he deems appropriate at any stage of the conciliation proceedings.

## ፷. ዕርቅ በሌሎች ሕጎች እንዲመራ የማይገደድ ስለመሆኑ

ተዋዋይ ወገኖች በተለየ ሁኔታ የሚያደርጉት ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዕርቅ በሌሎች መሠረታዊም ሆነ ሥነ-ሥርዓታዊ ሕጎች መሠረት እንዲመራ አይገደድም፡፡

## 60. Conciliation not Bound by Other Laws

Without prejudice to the agreement of the parties to the contrary, conciliation shall not be bound to be governed by any other substantive or procedural laws.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


## ፷፩. የአስታራቂው ሚና

፩/ አስታራቂው ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባታቸውን በስምምነት እንዲፈቱ ማገዝ አለበት፡፡

፪/ አስታራቂው ምክንያታዊነት እና ፍትሐዊነት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የተዋዋይ ወገኖችን መብት እና ግዴታ፣ ልማዳዊ አሠራርን እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል የነበረውን የቆየ የሥራ ወይም የንግድ ግንኙነት ጨምሮ አለመግባባቱን የሚመለከቱ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

፫/ አስታራቂው የጉዳዩን አካባቢያዊ ሁኔታ በቃል መስማትን ጨምሮ የተዋዋይ ወገኖች ፍላጎት እና አለመግባባቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍታት አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተስማሚ መስሎ በታየው ሁኔታ ዕርቁን ሊመራ ይችላል፡፡

፬/ አስታራቂው በየትኛውም የዕርቅ ደረጃ ላይ የዕርቅ ሀሣብ ሊያቀርብ ይችላል፣ የሚያቀርበው የዕርቅ ሀሳብ በጽሁፍ እንዲሆን እና ምክንያቱን እንዲገልጽ አይጠበቅበትም፡፡

## ፷፪. አስተዳደራዊ ድጋፍ ስለ መጠየቅ

ዕርቁን ለማመቻቸት ተዋዋይ ወገኖች ወይም አስታራቂው የተዋዋይ ወገኖችን ፈቃድ ሲያገኝ፣ አግባብነት ካለው ተቋም ወይም ግለሰብ አስተዳዳራዊ ድጋፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

## 61. The Role of the Conciliator

1/ The conciliator shall assist the contracting parties to resolve their dispute by maintaining his independence and impartiality.

2/ The conciliator shall, based on reasons and principles of justice, shall take into account the rights and duties of the parties, the customary practice and the circumstances surrounding the dispute including the long standing working or business relationship between the contracting parties,

3/ The conciliator may conduct the conciliation in a manner he considers appropriate by taking into account the interests of the contracting parties and the need for speedy resolution of the dispute including hearing oral statements about the circumstances surrounding the case.

4/ The conciliator may, at any stage of the conciliation proceedings, forward proposals for conciliation. He shall not be obliged to put his proposals in writing and provide reasons thereof.

## 62. Request for Administrative Support

The contracting parties or the conciliator upon obtaining the consent of the contracting parties to facilitate the conciliation, may seek administrative support from a relevant institution or individual.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



**፷፫. <u>በአስታራቂው እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ግንኙነት</u>**

፩/ አስታራቂው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በጋራ ወይም በተናጠል በቃል ወይም በጽሁፍ ግንኙነት ሊፈጥር ይችላል፡፡

፪/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር እና የዕርቁን አካባቢያዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚገናኙበትን ቦታ ይወስናል፡፡

**፷፬. <u>መረጃን ስለመግለጽ</u>**

፩/ የዕርቅ ስምምነቱን ለማስፈጸም መግለጹ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የዕርቅ ስምምነቱ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

፪/ አስታራቂው ከአንደኛው ተዋዋይ ወገን አለመግባባቱን በሚመለከት ያገኘውን መረጃ ለሌላው ተዋዋይ ወገን ሊገልጽለት ይችላል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም መረጃውን የሰጠው ወገን በምስጢር እንዲያዝለት የጠየቀ እንደሆነ አስታራቂው መረጃውን መግለጽ የለበትም፡፡

**፷፭. <u>ተዋዋይ ወገኖች ከአስታራቂው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ትብብር</u>**

ተዋዋይ ወገኖች በቅን ልቦና ከአስታራቂው ጋር የመተባበር፣ በአስታራቂው ሲጠየቁ ሰነዶችን እና ማስረጃዎችን የመስጠት እንዲሁም በውይይት ጊዜ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

**63. <u>Communication Between the Conciliator and the Parties</u>**

1/ The conciliator may, when he finds it necessary, communicate orally or in writing with the contracting parties together or with each of them separately.

2/ Unless there is an agreement made between the contracting parties, the conciliator shall, in consultation with the parties and by taking into account the circumstances surrounding the conciliation, determine the place of meeting.

**64. <u>Disclosure of Evidence</u>**

1/ Unless it is found to be necessary for the enforcement, the conciliation agreement shall be kept confidential.

2/ The conciliator may disclose to a contracting party the information that he has acquired about the dispute from the other party.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the conciliator shall not disclose the information if the party who gave the information has requested that it be kept confidential.

**65. <u>Co-operation of the Parties with the Conciliator</u>**

The parties shall co-operate with the conciliator in good faith, and shall, when requested by the conciliator, provide documents and evidence and attend meetings during discussion.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፷፮. በተዋዋይ ወገኖች የሚቀርብ የዕርቅ ሀሳብ**

እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከአስታራቂው በሚቀርብለት ጥያቄ አለመግባባቱን ለመፍታት የሚያስችል አስታራቂ ሀሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፷፯. በዕርቅ ስለሚደረግ ስምምነት**

፩/ አስታራቂው በተዋዋይ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል የዕርቅ ሀሳብ መኖሩን ሲያምን የማግባቢያ ሰነዱን አዘጋጅቶ ተዋዋይ ወገኖች እንዲያዩት ያደርጋል፤ በተዋዋይ ወገኖች የቀረብ ሀሣብ ካለ በቀረበው ሀሳብ መሠረት የማግባቢያ ሰነዱን ሊያስተካክል ይችላል፡፡

፪/ ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቱን ለመፍታት ከተስማሙ የዕርቅ ሰነድ በማዘጋጀት መፈራረም ይችላሉ፤ አስታራቂው በተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ከቀረበለት፣ የዕርቅ ስምምነት ሰነዱን ራሱ ሊያዘጋጅ ወይም ተዋዋይ ወገኖች የሚያዘጋጁት ከሆነ ሊያግዝ ይችላል፡፡

፫/ ዕርቅ የተደረገበት ስምምነት ውስጥ አንደኛው ወገን በሚያደርገው የመብት መተው ስምምነቱ የሚያስከትለው ውጤት በሌላኛው ወገን በኩል መብት መኖሩን መግለጽ ብቻ ነው፤ የተተወውን መብት ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ የችሎታና የፎርም ግዴታዎች ሊጠበቁ ይገባቸዋል፡፡

፬/ አስታራቂው የዕርቅ ስምምነት ሰነዱን በማረጋገጥ ቅጂውን ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን መስጠት ይኖርበታል፡፡

**66. Suggestions by the Contracting Parties for Conciliation**

Each party may, on its own initiative or upon request by the conciliator, submit suggestions for the settlement of the dispute.

**67. Settlement Agreement**

1/ Where the conciliator believes that there exists a proposal for conciliation that may be acceptable to the contracting parties, he shall formulate the terms of conciliation and submit them to the parties for their observations. The conciliator may modify the terms of the conciliation in line with the observations of contracting parties.

2/ Where the parties agree to resolve the dispute, they may draw up and sign a written settlement agreement. The conciliator may, if requested by the contracting parties, draw up, or assist the parties in drawing up, the settlement agreement.

3/ Waiver of a right by a contracting party under the settlement agreement shall only have effective only when the the other party states the existence of the right. The capacity and form requirements shall be observed for the transfer the waived right.

4/ The conciliator shall authenticate the settlement agreement and furnish a copy thereof to each contracting party.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


**፷፰. በዕርቅ የተደረሰው ስምምነት ውጤት እና አፈፃፀም**

የዕርቅ ሂደት ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ይግባኝ ሳይኖረው የመጨረሻ ሆኖ እንደተፈረደ ፍርድ ይሆናል፤ አፈፃፀሙም ለጉዳዩ የሥረ ነገር ሥልጣን ባለውና ስምምነት በተደረሰበት ቦታ በሚገኝ ፍርድ ቤት የሚከናወን ይሆናል፡፡

**፷፱. የዕርቅን ሂደት ስለማቋረጥ**

የዕርቅ ሂደት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይቋረጣል፡-

፩/ አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር ዕርቁን መቀጠል አላስፈላጊ ሆኖ ማግኘቱን ሲያሳውቅ፣

፪/ ተዋዋይ ወገኖች ዕርቁ መቋረጡን ለአስታራቂው በጽሁፍ ሲገልፁ፣

፫/ አንዱ ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን እና ለአስታራቂው ዕርቁን ስለማቋረጡ በጽሁፍ ሲገልጽ፣ ወይም

፬/ የዕርቅ ስምምነቱ ሲደረግ፡፡

**፸. ለፍርድ ቤት ወይም ለግልግል ዳኝነት ስለማቅረብ**

፩/ አስታራቂው በውል በተመለከተው የተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወይም ጊዜው ያልተወሰነ ከሆነ ከተመረጠበት ቀን ጀምሮ በ፮ ወር ጊዜ ውስጥ ተግባሩን መፈፀም ካልቻለ ወይም ዕርቅ ስላለመደረጉ አስታራቂው የጽሁፍ መግለጫ ካልሰጠ በቀር ተዋዋይ ወገኖች በዕርቅ የተያዘውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ግልግል ዳኝነት ለመውሰድ አይችሉም፡፡

**68. Effect and Enforcement of Settlement Agreement**

With regard to the subject matter of the agreement between the contracting parties, the settlement agreement shall be deemed to be final and non appealable decision. The execution shall be made by the court that has material jurisdiction and which is located at the place where the settlement agreement is reached.

**69. Termination of Conciliation Proceedings**

Conciliation proceedings shall be terminated under the following conditions:

1/ Where the conciliator in consultation with the parties declares that there is no need to continue with the proceedings;

2/ Where the parties notify the conciliator in writing that the conciliation is terminated;

3/ Where one of the parties notifies the other party and the conciliator in writing that he has terminated conciliation process; or

4/ Where the settlement agreement is made.

**70. Resort to Court or Arbitral Proceedings**

1/ Unless the conciliator, within the period specified under the agreement or where there is no specified time within 6 months from of his appointment or unable to perform the task or gave written declaration of unable to conclude the conciliation, the contracting parties shall not resort to the court or arbitral tribunal.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው ቢኖርም ተዋዋይ ወገኖች መብቶቻቸውን ለመጠበቅ ሲባል ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ ፍርድ ቤቱ እንዲሰጥላቸው ለማመልከት ይችላሉ፤ይህ ማመልከቻ የሚቀርበው የዕርቁ ሂደት እየተከናወነ ባለበት አካባቢ በሚገኝና ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው፡፡

## ፸፩. በዕርቅ የተደረሰውን ስምምነት ስለመቃወም

፩/ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ያደረጉባቸውን መብቶች በተመለከተ በተዋዋይ ወገኖች ወይም ከእነሱ ባንዱ በተደረገው ስህተት ምክንያት ስምምነቱን ለመቃወም አይቻልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዕርቅ ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ እንዲፈጸም በቀረበ ጊዜ ለመቃወም የሚቻለው ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ መኖሩን የቀረበው ስምምነት የተቃወመው ወገን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡

ሀ) ዕርቅ ለማድረግ የተደረገው ስምምነት ፈራሽ ወይም የማይፀና የሆነ እንደሆነ፤

ለ) የተደረሰው የዕርቅ ስምምነት ግልፅነት የጎደለው እንደሆነ፤

ሐ) የተደረገው ስምምነት ለመልካም ባህሪ ተቃራኒ ወይም የሕዝብን ሠላም እና ፖሊሲ የሚፃረር ከሆነ፤

መ) ተዋዋይ ወገኖች ስምምነቱን ለማድረግ የሚያስችለው ችሎታ የሌለው እንደሆነ፤

2/ Not withstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, contracting parties, with regard to their rights, may resort to the court to request for the order of interim measures. The request shall be submitted to a court located at the place where the settlement agreement is underway and that have material jurisdiction on the subject matter.

## 71. Objection of Settlement Agreement

1/ Objection shall not be raised, in relation to the rights that are reached settlement agreement on the ground of mistake committed by the parties or by one of them.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, an objection to the execution of the settlement agreement may only made where the existence of the following grounds is ascertained by the party who objects the settlement agreement.

a) The settlement agreement is null and void;

b) The settlement agreement lacks clarity;

c) The settlement agreement is contrary to good conduct or violates public peace and policy;

d) Contracting parties lacks capacity to conclude the agreement.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፫/ በመሠረታዊ ስህተት የተነሳ ስምምነት የተደረሰበትን ዕርቅ ለማፍረስ የሚቻለው ለመፈጸም ግዴታ የገቡበት ሰነድ እራሱ ፈራሽ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

፬/ ተዋዋይ ወገኖች ወይም ከተዋዋዮቹ የአንዱ ፈቃድ የተገኘው ሐሰተኝነቱ በታወቀ ሰነድ መሠረት እንደሆነ ስምምነቱን ለማፍረስ ይቻላል፡፡

፭/ በውሉ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖች ሰነዱ ፈራሽ ወይም ሐሰተኛ እንደሚሆን አስበው የተስማሙ እንደሆነ ስምምነቱ እንደፀና የሚቀር ይሆናል፡፡

## ፸፪. የዕርቅ ስምምነት አተረጓጎም

ዕርቅ የተደረሰበት ስምምነት ጠባብ በሆነ መልኩ መተርጎም አለበት፡፡

## ፸፫. የዕርቅ ሂደት ወጪ እና ክፍያ

፩/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ የውል ስምምነት ከሌለ በስተቀር አስታራቂው ለዕርቁ ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን ካልሆነ በስተቀር ለአገልግሎቱ የሚከፈለው ክፍያ አይኖርም፡፡

፪/ የዕርቁ ሂደት ሲቋረጥ አስታራቂው የዕርቅ ወጪ በመወሰን ለተዋዋይ ወገኖች በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ወጪ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በአስታራቂው እና በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ አስታራቂው ለጠራቸው ምስክሮች የሚከፈል ክፍያ እና ወጪ፤

3/ The settlement agreement may be invalidated on the ground of fundamental error where the document obliged the parties itself is null and void.

4/ The settlement agreement may be invalidated where the consent of the contracting parties or one of them is obtained by a document which proved to be false.

5/ The settlement agreement shall remain valid where the contracting parties aware that the document is void or false.

## 72. Interpretation of Settlement Agreement

Settlement agreement shall be interpreted in a narrow manner.

## 73. Cost of Conciliation and Payment

1/ Unless the parties agree otherwise, no payment shall be made to the conciliator for his service except for reimbursement of expenses incurred for the purpose of conciliation.

2/ The conciliator shall, upon termination of the conciliation proceedings, determine the cost incurred and notify the same to the contracting parties.

3/ The cost stated in Sub-Article (2) of this Article shall include the following:

a) Payments made and costs incurred for witnesses summoned by the conciliator with the consent of the conciliator and the contracting parties;

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


ለ) በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ በአስታራቂው ጠያቂነት በሙያተኛ ለተሰጠ ሙያዊ አስተያየት ወይም ምክር የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለተሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

መ) ሌሎች ከዕርቅ ሂደት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች እና ክፍያዎች፡፡

፬/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ ወጪዎች እና ክፍያዎች በተዋዋይ ወገኖች በጋራ ይሸፈናሉ፤ ሆኖም ወጪው አንደኛውን ተዋዋይ ወገን ብቻ የሚመለከት ከሆነ ወጪው በዚሁ ተዋዋይ ወገን ይሸፈናል፡፡

**፸፬. ክልከላ**

በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፡-

፩/ አስታራቂው በዕርቅ በያዘው ጉዳይ በማንኛውም የግልግል ዳኝነት ወይም የፍርድ ሂደት ላይ የግልግል ዳኛ፣ ጠበቃ ወይም ወኪል በመሆን መሥራት፤

፪/ በማንኛውም የግልግል ዳኝነት ወይም የፍርድ ሂደት ላይ በተዋዋይ ወገኖች ምስክር ሆኖ መቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

**፸፭. በማስረጃነት መቅረብ ስለማይችሉ ጉዳዮች**

ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በታች የተመለከቱትን በግልግል ዳኝነት ወይም በፍርድ ሂደት በማስረጃነት ማቅረብ አይችሉም፡-

፩/ አለመግባባቱን በዕርቅ ለመፍታት በማሰብ በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ አስተያየት ወይም ሀሳብ፤

b) Service charge for expert opinion or advice provided by an expert upon the request of the conciliator with the consent of the contracting parties;

c) Payments made for services rendered in accordance with this Proclamation;

d) Other expenses incurred, and payments made, in connection with the conciliation proceedings.

4/ Unless the contracting parties agree otherwise, the costs and payments shall be borne jointly by the parties. However, expenses related to one of the parties shall be borne by that party.

**74. Prohibition**

Unless the parties agree otherwise, a conciliator shall be prohibited from:

1/ Acting as arbitrator, attorney or agent in any arbitration or judicial proceeding in matters related to the conciliation handled by him;

2/ Appearing as a witness before any arbitration or judicial proceeding for the contracting parties.

**75. Matters Inadmissible as Evidence**

The contracting parties shall be prohibited to submit the following as evidence: in arbitral or judicial proceedings:

1/ Suggestions or views forwarded by one of the contracting parties with the intention of settling a dispute;

፪/ በዕርቅ ሂደት በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ የእምነት ቃል፤

፫/ በአስታራቂው የቀረበ የዕርቅ ሀሳብ እና በአስታራቂው የቀረበውን የዕርቅ ሀሳብ ለመቀበል በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ ፈቃደኝነት፡፡

**፸፮. የዳኝነት ክፍያ ስለመመለስ**

፩/ ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እንዲታይ ክስ መስርተው ከነበረ እና ክሱን በመተው ጉዳያቸውን በዕርቅ ከጨረሱ ለፍርድ ቤት የከፈሉት የዳኝነት ክፍያ እንደ አግባብነቱ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዝርዝር አፈፃፀም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሠናል፡፡

**ክፍል አስር**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፸፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈረሙ የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በነበሩ ሕጎች መሠረት የሚገዙ ይሆናል፡፡

፪/ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጀመሩ የግልግል ዳኝነቶች ወይም የግልግል ዳኝነትን በተመለከተ በፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች፣ የክርክር ሂደቶች እና የተሰጡ ውሳኔዎች አፈጻጸም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በነበሩ ሕጎች መሠረት ይታያሉ፡፡

2/ An admission made by one of the contracting parties in the course of conciliation proceedings;

3/ A settlement proposal submitted by a conciliator and the consent of one of the party to such proposal.

**76. Reimursment of Court Fee**

1/ Where the contracting parties had instituted a suit in a court and have resolved their dispute through conciliation by withdrawing their suit, the court fee shall where appropriate be reimbursed to them.

2/ The details for the implementation of the provisions of Sub-Article (1) of this Article shall be provided for in a Regulation to be issued by the Council of Ministers.

**SECTION TEN**

**MISCELLENOUS PROVISIONS**

**77. Transitional Provisions**

1/ Any arbitration agreement signed before the coming into force of this Proclamation shall be governed by the law that had been in force before the effective date of this Proclamation.

2/ Arbitral proceedings initiated before the coming into force of this Proclamation or cases of arbitration pending before courts, ongoing proceedings and execution of decisions shall be governed by the law in force before the coming into force of this Proclamation.

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief



፫/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የግልግል ዳኝነት ስምምነት የፈፀሙ ወይም በሂደት ላይ ያሉ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አዋጅ መሠረት ለመዳኘት መስማማት ይችላሉ፡፡

**፸፰. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ ከአንቀጽ ፫ሺ፫፻፲፰ እስከ ፫ሺ፫፻፳፬ ስለ ዕርቅ የተደነገጉት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እና ከአንቀፅ ፫ሺ፫፻፳፭ እስከ ፫ሺ፫፻፵፮ ስለ ዘመድ ዳኛ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ የዘመድ ዳኛን የተመለከቱት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከአንቀፅ ፫፻፲፭ እስከ ፫፻፲፱፣ ፫፻፶፣ ፫፻፶፪፣ ፫፻፶፭-፫፻፶፯ እና ፬፻፷፩ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፫/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፸፱. <u>ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው ሕጎች</u>**

የዕርቅ ወይም የግልግል ዳኝነት ሂደቱን ለማከናወን የሚረዱ ወይም ከሂደቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ይህንን አዋጅ የማይቃረኑ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

3/ Contracting parties who have concluded arbitration agreement or in the process concluding an agreement before the coming into force of this Proclamation may agree to be governed by this Proclamation.

**78. <u>Inapplicable Laws</u>**

1/ The provisions of Articles 3318 to 3324 of the Civil Code which deals about conciliation and the provisions Articles 3325 to 3346 of the Civil Code which deals about arbitrator shall be repealed by this Proclamation.

2/ The provisions of the civil procedure code from Articles 315 to 319,350,352,355-357 and 461 which deals about arbitrator repealed by this Proclamation.

3/ Other law or customary practices that are inconsistent with this Proclamation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

**79. <u>Applicable Laws</u>**

The Provisions of the Civil Procedure Code that may help the implementation of the conciliation or arbitration proceedings or related to the proceedings and not contravene this Proclamation shall be applicable.

**፹. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትሎ የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

**፹፩. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**80. Power to Issue Regulations And Directive**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ Federal General Attorney may issue Directive to implement this Proclamation or the Regulation to be issued to implement this Proclamation.

**81. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force from the date of its publication in Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 2nd Day of April 2021.**

**SAHELEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**